# ኢት-ኢኮኖሚ /ET- ECONOMY

*‹‹ኢኮኖሚውን ካላወቁ፣ፖለቲካውን አይነቀንቁ!!!››*

ወት ጊዩን ዘ/ማርያም

## ክፍል አንድ

## ‹‹አህያ የተጫነችውን አትበላም!!!››

(ለኢትዩጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ምላሽ እንዲሠጡበት የቀረበ የኢት-ኢኮኖሚ ጥናታዊ ዳሰሳ)

### የኢት-ኢኮኖሚ መግቢያ

*የአንድ አገር ኢኮኖሚ የሃገሪቱ ፖለቲካ ነፀብራቅ ነው!!!ለዚህ ነው ‹‹ኢኮኖሚውን ካላወቁ፣ፖለቲካውን አይነቀንቁ!!!››* የሚባለው፡፡ የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግሥት በ1997ዓ/ም በምርጫ ወድቆ ነበር፣ በ2008ዓ/ም ህዝባዊ እንቢተኝነትና ተጋድሎ ዳግም ወድቆ ነበር፡፡ የቻይና መንግስት የህወሓት መንግስት እንዳይወድቅ የማያገላብጠው ድንጋይ የለም፡፡ ኢትዩጵያ በቻይና ስውር ቅኝ አገዛዝ ስር ከወደቀች ቆይታለች፣ የቻይና ኮምኒስት ፓርቲ ለህወሓት መንግስት 17.5 ቢሊዩን ዶላር ብድር አበድረዋል፡፡ እንዲሁም ቻይና መንግሥትና የግሉ ዘርፍ በኢትዩጵያ ውስጥ 17.6 ቢሊዩን ዶላር ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት አድርገዋል በማድረግም ላይ ናቸው፡፡ አበው ሲተርቱ ‹‹አህያ የተጫነችውን አትበላም!!!›› ይላሉ፡፡ የአህያው ነጂ የቻይና መንግሥት፣ አህያው የህወሓት መንግስት እንዲሁም አህያዋ የተጫነችው እህል፣ የኢትዩጵያ ህዝብ የተዘረፈው አንጡራ ኃብት መሆኑን አንርሳ፡፡ የቻይና መንግሥት በቅርቡ በህወሓት መንግስት ላይ የብድር አልከፈላችሁም ትልቅ ጫና በመፍጠር የፕራይቬታይዜሽን መርሃ-ግብር ለሁለተኛ ግዜ በመንደፍ፣ የመንግሥት ልማታዊ ድርጅቶች ማለትም የኢትዩጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ መብራት ኃይል፣ አየር መንገድ፣ ንግድ መርከብ፣ የምድር ባቡር፣ ድርጅቶች ንብረት ባለባቸው የቻይና መንግስት ዕዳ የተነሳ፣ በፕራይቬታይዜሽን ስም ቀስ በቀስ ወደ ቻይና መንግሥትና የግሉ ዘርፍ ንብረትነት ይዘዋወራሉ፡፡ በኢትዩጵያ ውስጥ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ደካማነት፣የገበያ ውድድር ያለመኖር፣የመዋለ-ንዋይ ፍሰት ደካማነት፣ የፋይናንሻል ሃብት እጥረት፣የውጪ ንግድ ዘርፍ ገቢ የመነመነ መሆን፣ የውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጫወተው ሚና ደካማነት ወዘተ ተደማምሮበት የመንግስታዊ ልማታዊ ድርጅቶች ያለባቸውን እዳ ለመክፈል ስለማይችሉ የፕራይቬታይዜሽን ሽግግር ወደ ቻይና መንግሥትና የግሉ ዘርፍ ግድ ይላል ማለታቸው አይቀሬ ነው፡፡ ቻይና በሃገሮ ውስጥ 400 ሚሊዩን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ነው የሚኖረው፡፡ ህዝባቸውን መታደግ ግድ ይላቸዋል፡፡ ሌሎቹም አሜሪካና የአውሮፓ ህብረት አገራቶች በኢትዩጵያ ያላቸው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅምን በመገንዘብ እነሱ ይረዱናል ብለን አለመዘናጋት ያስፈልጋል፡፡ በኢትዩጵያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ እንቢተኝነታና ተጋድሎ ከፍ ወዳለ እርከን ተሸጋግሮል ህዝቡ በራሱ በሚስጢር እየተደራጀና እየታጠቀ፣በእራሱ የመተማመን ኃይሉን እያጠናከረ፣ በዱር በገደሉ ፋኖ ሆኖል፡፡ የኢትዩጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎችና ድርጅቶች ህብረት ፈጥረው በየቦታው ያለውን ህዝባዊ ኃይል በመርዳትና በማስተባበር ከገጠር ወደ ከተማ በተቀናጀ የጎሬላ ደፈጣ ውጊያ ሥልት በመጠቀም የህዝባዊ ሠራዊት በመላ ሃገሪቱ በመገንባት ለድል መብቃቱ አይቀሬ ነው፡፡ በኦጋዴን፣በአፋር፣በአማራ፣በኦሮሚያ፣በጋምቤላ፣በትግራይ፣ወዘተ የተቀጣጠለው ህዝባዊ ፋኖነት የቻይና ድራጎኖችንና የደደቢት ወያኔዎችን ይደመስሳል፡፡ የህዝብ ድጋፍ የሌለው መንግስት መውደቁ አይቀሬ ነው፡፡ በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙትን ወንድምና እህቶቻችንን አፈሙዛቸውን ወደ ወያኔ እንዲያዞሩና ህዝባዊውን ትግል እንዲቀላቀሉ ማድረግ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡

## የ2008ዓ/ም ብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) ስምንት በመቶ ዕድገት እንዳሳየ ተገለፀ

እርግጠኛ ብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት (Real GDP) እና ምስለ ብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት (Nominal GDP) በምርትና የገንዘብ ምጣኔን፣ የብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ይናገር ደሴ ከመግለፅ ተቆጥበዋል፡፡

‹‹የሃገር ውስጥ ምርት በገንዘብ ዋጋ በሁለት መልክ ይለካል፣ አንደኛው ምርቱ በተመረተበት ዓመት የገበያ ዋጋ መለካት ነው፡፡ ሁለተኛው የዋጋ ንረትን በምርቱ ዋጋ ውስጥ ላለማስገባት በአንድ በተመረጠ ዓመት ቋሚ ዋጋ አማካኝነት የተከታታይ ዓመታት ምርት ይለካል፡፡››

- ምስለ ብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት (Nominal GDP) ምርቱ በተመረተበት ዓመት የገበያ ዋጋ (Current Market Price) መሠረት የለካል፡፡ በየአመቱ የሚከሰተውን የዋጋ ንረት የሚጨምር ስለሆነም በዋጋ ንረት ተበክሎ ያበጠ ምርት ነው፡፡
- እርግጠኛ ብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት (Real GDP) በአንድ የተመረጠ ዓመት የቀድሞ ቋሚ የገበያ ዋጋ (Constant Market Price) መሠረት የለካል፡፡ በየዓመቱ የሚከሰተውን የዋጋ ንረት ስለማይጨምርም በዋጋ ንረት ያልተበከለና ያላበጠ ምርት ነው፡፡
- ማሳሰቢያ፡- በኢትዮጵያ እስከ 2003ዓ/ም ድረስ እርግጠኛ አማካይ ዓመታዊ ጠቅላላ የሃገር ውስጥ ምርት (Real GDP) በ1992 ዓ/ም ቋሚ የገበያ ዋጋ መሠረት ሲለካ ነበር፡፡ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ ግን መለኪያ ዋጋው ወደ 2003 ዓመት የገበያ ዋጋ ተከልሷል፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) በቢሊዮን ዶላር
ከ2009 እስከ 2015 እኤአ

| ዓመት (እኤአ) | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | | 2014 | 2015 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዩኤስ ቢሊዮን ዶላር | 32,189.0 | 29,706.2 | 31,708.8 | 43,133.1 | 55.6 | | 51.0 | 69[1] |

69[1] ታህሣሥ 3 ቀን 2009 ዓ/ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገፅ 2 የተገኘ መረጃ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) 32,189.0 ቢሊዮን ዩኤስ ዶላር በ(2009 እኤአ), USD$ 29,706.2 ቢሊዮን ዶላር በ(2010እኤአ), USD$ 31,708.8 ቢሊዮን ዶላር በ(2011እኤአ), USD$ 43,133.1 ቢሊዮን ዶላር በ(2012እኤአ), USD$ 51.0 ቢሊዮን ዶላር በ(2014እኤአ) እንዲሁም 69 ቢሊዮነረ ዶላር በ(2015 (እኤአ)፣የአለም ባንክ የዓለም እድገት ጠቆሚ /ዩኤንዲፒ የሰው ኃይል ልማት ሪፖርት/የዓለም የገንዘብ ድርጅት/የዓለም ዓቀፍ ኢኮኖሚ ሪፖርት መሠረት፣በ2013እኤአ የተጠናከረ መረጃ ነው፡፡

- GDP: USD$ 32,189.0 (2009), USD$ 29,706.2 (2010), USD$ 31,708.8 (2011), USD$ 43,133.1 (2012), USD$ 51.0 (2014), (source: The World Bank, World Development Indicators 2013/ UNDP, Human Development Report 2013/ International Monetory Fund (IMF) / World Economy Outlook 2013)
- The Ethiopian fiscal year runs from July 8 to July 7.

## {I} የኢትዮጵያ ብሄራዊ ኢኮኖሚ በ2008 ዓ/ም

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የኢኮኖሚ ገቢው ፈጣን እድገት ማሳየቱን የብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ይናገር ደሴ አስታውቀዋል፡፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የተገኘው ገቢ ስምንት በመቶ እድገት አሳይቶል፡፡ ባለፈው አመት የተከሰተውን ከባድ ድርቅ መቋቋም የተቻለው የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ገቢዎች ዕድገት በማሳየታቸው ነው፡፡ የግብርናው ዘርፍ በ2003 ዓ/ም ከነበረበት 44.4 በመቶ ወደ 36 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከ10.4 በመቶ ወደ 16.6 በመቶና የአገልግሎት ዘርፍ ከ45.2 በመቶ ወደ 47.0 በመቶ ከፍ ማለቱን ኮሚሽነሩ አክለው ገልፀዋል፡፡

### Nation’s economy upright even in tides

*‘‘The national planning Commission said the country has registered 8 per cent economic growth amid shaky global market and El Nino induced drought.*

*Commissioner Dr.Yenager Dessie said resisting all internal and external economic problems; the country registered 8.0 per cent economic growth. He said agriculture marked a 2.3 per cent growth while the service sector by 8.7 per cent.*

*According to him, the industrial sector stands high compared to sectors registering over 20.6 per cent growth. The structure of the economy has shown some shift from agriculture to service and industrial sectors.*

*Accordingly, the real GDP share of agriculture declined from 44.4 six years ago to 36.4 per cent last fiscal year. The share of the industry shows a surge to 16.6 the same fiscal year from 10.4 six years ago and that of service to 47.0 from 45.2.*
*The country's economy registered an average of 9.8 per cent successive growth annually over the last six years. Similarly, major sectors- agriculture, industry and service average growth stands at 5.9, 20.0 and 10.6 per annum respectively.*
*Per capita income increased to 794 USD from 725 in 2015, while saving reached 22.4 per cent of the GDP. Attributing unstable foreign market as barrier export has accounted 8.0 per cent of the GDP and import 27.8 per cent.*
*"Last fiscal year's growth proved commendable transformation towards manufacturing industry. This fiscal year, the nation has planned to achieve better growth in all sectors" indicating ongoing construction of 12 industrial parks the nation, the commissioner expressed conviction that export trade would show increase this fiscal years. "The fiscal year, Ethiopia envisages 11 per cent economic growth."*

- 2015/16) ብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት ስንት እንደሆነ አልተገለጸም።
- የግብርና ዘረፍ እድገት 2.3 በመቶ (2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት እንደሆነ ተገልጾል።
- የኢንደስትሪ ዘርፍ፣እድገት 20.6 በመቶ(2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት እንደሆነ ተገልጾል። ሆኖም ከግብርናው ዘርፍ ወደ ኢንደስትሪው ዘርፍ የገባ የሰው ኃይል ወይም ገበሬው ወደ ወደ ላብአደርነት መዘዋወሩን አያመላክትም።
- የአገልግሎት ዘረፍ እድገት 8.7 በመቶ (2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት እንደሆነ ተገልጾል።ሆኖም ከግብርናው ዘርፍ ወደ አገልግሎቴ ዘርፍ የገባ የሰው ኃይል መዘዋወሩን አያመላክትም።
- የፊዝካል ዲፊሲት አስተዋጽኦ በመቶ(2004/5) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት ስንት እንደሆነ አልተገለጸም።
- የውጭ ንግድ(ኤክስፖርት) ዘረፍ አስተዋጽኦ 2.86 ቢሊዮን ዶላር (2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት እንደሆነ አልተገለፀም ከሌላ ምንጭ የተገኘ ነው። የውጭ ንግድ (ኤክስፖርት) ዘረፍ 8.0 በመቶ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ እንዳለው ገልጾዋል። ትልቅ ውሸት ነው እውነቱ እንሆ የውጭ ንግድ (ኤክስፖርት) ዘረፍ (2.86/69 ሲባዛ በ100) 4.1 በመቶ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ እንዳለው ታውቆል። የ2015/16እኤአ ጅዲፒ 69 ቢሊዮን ዶላር ተብሌ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የተገኘ መረጃ መሠረት በማድረግ የተሰላ ነው።
- ከሪፖርተር ጋዜጣ መረጃ መሠረት የገቢ ንግድ (ኤንፖርት) ዘረፍ አስተዋጽኦ 22.0 ቢሊዮን ዶላር (2015/16) ተገልጾል። ስለዚህ የገቢ ንግድ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት (22/69 ሲባዛ በ100) 31.8 በመቶ እንደሆነ በስሌት ይታያል። የገቢ ንግድ (ኤንፖርት) ዘረፍ 27.8 በመቶ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ እንዳለው የተገለፀው ውሸት እንደሆነ መረዳት ችለናል።
- የንግድ ሚዛን ኪሳራ -19140000 ቢሊዮን ዩኤስ ዶላር (2015/16) ስናሰላው ይስተዋላል። መረጃ ድብቅ በሆነበት አገር ለተማሪዎች የሃሰት የኢኮኖሚክስ ትምህርትና ምናባዊ ዓሃዞች በመደርደር፣ በሁለት አሃዝ አደግን እያሉ የወያኔ ካድሬ ሹመምንቶች እንደ ጀግንነት ትውልዱን እውሸት ያስተምራሉ። ሁሌ አገራችን ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም እንትንኛ እያሉ ይቀጥፋሉ። በአትሌቲክስ ብቻ እስካልሆነ በስተቀር በኢኮኖሚው እንኳን አንታማም።
- አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ (Per capita income) 794 ዶላር (2015/16) እንደሆነ ተገልጾል። በኢትዩጵያ የአንድ ሰው የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ 17849 (የአንድ ዶላር ምንዛሪ በ22.48 ብር) ብር ሆኖ እናገኘዋለን። ወራዊ ገቢውን ለማወቅ በ12 ወራቶች ስናካፍለው 1487 ብር ሆኖ እናገኘዋለን። ይሄም መረጃ በቅጥፈት ላይ የተመሠረተ ነው በአማካይ በወር 1487 ብር የሚያገኝ ዜጋ በጣም ጥቂት ነው።
- የአገር ውስጥ ቁጠባ (saving) 22.4 በመቶ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ እንዳለው ተገልጾል። ይሄ ማለት የአገር ውስጥ ቁጠባ 15.456 ቢሊዮን ዶላር ሆኖል ነው የሚሉን 15.456 ሲካፈል 69 ቢሊዮን ዶላር ሲባዛ 100 ይሆናል 22.4 በመቶ ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ምሁሮች ከየት ተፈለፈሉ? በ2011 እኤአ የዓለም ባንክ ሪፖርት መሠረት ከ1980/81 እስከ 2010/11 እኤአ የኢትዩጵያ አማካኝ የሃገር ውስጥ ቁጠባ መጠን 8.6 በመቶ ከአመታዊ ብሄራዊ ምርት (ጂዲፒ) ድርሻ የነበረ ሲሆን በተመሳሳይ አመታት ከሳህራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራቶች አማካኝ የሃገር ውስጥ ቁጠባ መጠን 17.2 በመቶ ከአመታዊ ብሄራዊ ምርት (ጂዲፒ) ድርሻ ነበራቸው። በዚህም የተነሳ የኢትዩጵያና ከሳህራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራቶች አማካኝ የሃገር ውስጥ ቁጠባ መጠን ከአመታዊ ብሄራዊ ምርት (ጂዲፒ) ድርሻ በጣም ዝቅተኛ ነበር። Moreover, available data from World Bank report (2011) shows that the average saving rate of Ethiopia was very low by any standard. For instance, when compared with the average saving rates of Sub-Saharan Africa countries between the period 1980/81 and 2010/11, average

domestic saving rate in Ethiopia was only 8.6% of the GDP. However, during the same period, the average for Sub-Saharan Africa countries was 17.2% of GDP. This implies how much the domestic saving rates of Ethiopia were too much low even by Sub-Saharan Africa standards.

- የኢንቨስትመንት ዘረፍ አስተዋጽኦ በመቶ(2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ እንዳለው አልተገለጸም፡፡
- የፊዝካል ዲፊሲት አስተዋጽኦ ልዩነት በመቶ(2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት ስንት እንደሆነ አልተገለጸም፡፡ እንዲሁም መንግስታዊው ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች ከባንኮች ብድር እየጨመረ መሄድና በሃገሪቱ ኢንቨስት በማድረግ ከፍተኛውን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ መንግስት ዘርፍ፣ ከፍተኛውን ኢንቨስትመንት በማድረግ የሃገር ውስጥ ብድርና የውጭ ሃገር ብድር ስንት ቢሊዩን ዶላር እንደደረሰ በሪፖርቱ አልተካተተም፡፡
- ለማጠቃለል፤ የአገር ውስጥ ቁጠባ ከፍተኛው እድገት 22.4 በመቶ(2015/16) ሲሆን የኢንቨስትመንት ዘረፍ አስተዋጽኦ እድገት በመቶ (2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት ስንት እንደሆነ አልተገለጸም፡፡ ስለዚህም የፊዝካል ዲፊሲት አስተዋጽኦ ልዩነት በመቶ(2015/16) ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት እድገት እንደሆነ ማስላት አልተቻለም፡፡ ሆኖም መንግስታዊው ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች ከባንኮች ብድር እየጨመረ መሄድና በሃገሪቱ ኢንቨስት በማድረግ ከፍተኛውን ሚና በመጫወት ላይ መሆናቸው በኢኮኖሚ አጥኚዎች ዘንድ በማስረጃ ተረጋግቶል፡፡ የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት መንግስታዊ ዘርፍ፣ኢፈርት፣ሜቴክ፣ መከላከያ ኮንስትራክሽን፣መንግሥታዊ የልማት ድርጅቶች(የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣የኢትዮጵያ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር፣የኢትዮጵያ መብራት ኃይል፣ የስኳር ኮርፖሬሽን፣የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ወዘተ) እንዲሁም የተለያዩ የፓርቲዎች የኢኮኖሚ ኢፓየር በሞኖፖል ከፍተኛውን ኢንቨስትመንት በማድረግ የሃገር ውስጥ ብድርና የውጭ ሃገር ብድር 35-45 ቢሊዩን ዶላር መድረሳቸው በጥናት በማስረጃ ተረጋግጦል፡፡

| ዓመት | ግብርና ዘርፍ | ኢንደስትሪው ዘርፍ | አገልግሎት ዘርፍ | በመቶ |
|---|---|---|---|---|
| 1960 | 75.8 | 7.0 | 17.2 | 100 |
| 1991 | 56.5 | 9.0 | 34.5 | 100 |
| 2011 | 46.6 | 14.5 | 38.9 | 100 |
| 2013/14 | 42.0 | 13.0 | 45.0 | 100 |
| 2014/15 | 40.0 | 14.0 | 46.0 | 100 |
| 2015/16 | 38.8 | 15.2 | 46.6 | 100 |
| 2016/17 | 36.4 | 16.6 | 47.0 | 100 |

- በ1960 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 75.8 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 7.0 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 17.2 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር፡፡
- በ1991 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 56.5 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 9.0 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 34.5 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር፡፡
- በ2014/15 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 40.0 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 14.0 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 46.0 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር፡፡
- በ2015/16 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 36.4 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 16.6 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 47.0 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር፡፡

| ተ/ቁ | የኢኮኖሚ ዘርፍ | ዓ/ም 2003 | ዓ/ም 2007/08 | የ2007/08 ዓ/ም ብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት 69 ቢሊዩን ዶላር የዘርፎቹ ድርሻ | በኢኮኖሚ ዘርፉ የተሰማራ የሰው ኃይል በመቶኛ በ2007እኤአ ግምት Labour force by occupation 2007 Estimate | በዘርፉ የተሰማራ የሰው ኃይል በሚሊዩን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና | 44.4% | 36.4% | 25.1 ቢሊዩን ዶላር | 85% | 32.2 |
| 2 | ኢንዱስትሪ | 10.4% | 16.6% | 11.5 ቢሊዩን ዶላር | 5% | 1.9 |
| 3 | አገልግሎት | 45.2% | 47.0% | 32.4 ቢሊዩን ዶላር | 10% | 3.8 |
| | ደምር | 100% | 100% | 69 ቢሊዩን ዶላር | 100% | 37.9 |

**Labour force** 37.9 million 2007 Estimate

69[1] ታህሣሥ 3 ቀን 2009 ዓ/ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገፅ 2 የተገኘ መረጃ

በጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊና ኃይለማርያም ደሣለኝ ዘመነ መንግስት

በ1991 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 56.5 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 9.0 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 34.5 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር።
በ2014 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 40.0 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 14.0 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 46.0 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር።
በ2015/16 እኤአ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርናው ዘርፍ 36.4 በመቶ፣በኢንደስትሪው ዘርፍ 16.6 በመቶና በአገልግሎት ዘርፍ 47.0 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፆኦ ያደርግ ነበር። አንባቢ ማስተዋል ያለበት በግብርና፣ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፎች ድርሻ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ያደረጉት ድርሻ ዝግምተኛ ለውጥ እንደሆነና ለምን ኢንዱስትሪው በዝግምተኛ እድገት ውስጥ ይኮትናል?

| EPDRF REGIME | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **Year** | **GDP (in millions of Birr)** | | | | **Percentage of the GDP (%)** | | | |
| Political Regime | Agriculture | Industry | Services | Total | Agriculture | Industry | Service | Total |
| 1991 | 5,947.60 | 951.28 | 3,635.73 | 10,534.61 | 56.5 | 9.0 | 34.5 | 100 |
| 1992 | 6,308.32 | 1,221.90 | 4,268.57 | 11,798.79 | | | | |
| 1993 | 6,078.00 | 1,307.05 | 4,614.20 | 11,999.25 | | | | |
| 1994 | 6,284.00 | 1,412.54 | 4,947.81 | 12,644.35 | | | | |
| 1995 | 7,206.20 | 1,488.87 | 5,292.01 | 13,987.08 | | | | |
| 1996 | 7,453.90 | 1,530.57 | 5,655.80 | 14,640.27 | | | | |
| 1997 | 6,620.60 | 1,566.60 | 6,241.90 | 14,429.10 | | | | |
| 1998 | 6,873.50 | 1,700.90 | 6,719.70 | 15,294.10 | | | | |
| 1999 | 7,024.70 | 1,731.30 | 7,356.34 | 16,112.34 | | | | |
| 2000 | 7,831.10 | 1,821.40 | 7,705.20 | 17,357.70 | | | | |
| 2001 | 7,651.00 | 1,864.00 | 8,057.80 | 17,572.80 | | | | |
| 2002 | 6,687.00 | 1,943.40 | 8,252.70 | 16,883.10 | 39.6 | 11.5 | 48.9 | 100 |
| 2003 | 7,953.80 | 2,080.60 | 8,783.80 | 18,818.20 | 42.3 | 11.0 | 46.7 | 100 |
| 2004 | 9,154.80 | 2,228.60 | 9,349.30 | 20,732.70 | 44.2 | 10.7 | 45.1 | 100 |
| 2013/14 | | | | | 42.0 | 13.0 | 45.0 | 100 |
| 2014/15 | | | | | 40.0 | 14.0 | 46.0 | 100 |
| 2015/16 | | | | | 36.4 | 16.6 | 47.0 | 100 |

በ1996/97 እኤአ የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ ኢኮኖሚ ለገጠሩ ህዝብ 81 በመቶ የሥራ እድልና መተዳደሪያ ገቢው ሲሆን ቀሪው 19 በመቶ የከተማ ህዝብ ሲሆን በኢንደስትሪና አገልግሎት ዘርፎች የሥራ እድል በማግኘት የሚተዳደር እንደሆነ በጥናት ተረጋግጦል። በ2010/11 እኤአ የግብርና ዘርፍ ኢኮኖሚ ለገጠሩ ህዝብ 78 በመቶ የሥራ እድልና መተዳደሪያ ገቢው ሲሆን ቀሪው 22 በመቶ የከተማ ህዝብ ሲሆን በኢንደስትሪና አገልግሎት ዘርፎች የሥራ እድል በማግኘት የሚተዳደር እንደሆነ በጥናት ተረጋግጦል። ከ1996 እስከ 2010እኤአ ባለው 14 አመታት ውስጥ ከግብርና ዘርፍ ኢኮኖሚ (81%-78%) 3% በመቶ የሥራ ዕድል ለከተማ ውስጥ የኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፍ አበርክቶል።
- Share of the population employed primarily in the agricultural sector has only fallen from 81% in 1996/97 to 78% in 2010/11(**UNDP - Ethiopia HDR 2015 (Human Dev. Report)**
http://hdr.undp.org/sites/default/fi...thiopia-en.pdf)

ከሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የግብርና ዘርፍ ኢኮኖሚ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት በ1991እኤአ (56.5በመቶ) ወደ 2014 (40 በመቶ) ዝቅ ቢልም የገጠሩ ህዝብ ቁጥር 3 ከመቶ ብቻ የቀነሰው። በሌላ አነጋገር የገጠሩ ህዝብ ወደ ከተማ 3 በመቶ ያህል ብቻ ነው የገባው። ከ1991 እስከ 2014 እኤአ ባለው 23 ዓመታቶች ውስጥ ከግብርናው ዘርፍ፣ የሰው ኃይል ወደ በኢንደስትሪና አገልግሎት ዘርፎች የተወሰዱ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ መሆን የተስተካከለ የኢኮኖሚ እድገት እንደሌለ ያመላክታል ወይም መዋቅራዊ ለውጥ/መሠረታዊ ለውጥ (Structural Transformation) የህልም እንጀራ ሆኖል ማለት ነው። በሌሎች አገራቶች ልምድ የግብርናው ዘርፍ እየቀነሰ በሄደ ቁጥር የኢንዱስትሪ ዘርፉ እድገት በተመጣጣኝ እያደገ ይሄዳል ገበሬው ወዛደር እየሁነ ይሄዳል፣ ከገጠሩ ህዝብ የተቀነሰው ወደ ከተመው ህዝብ እየፈለሰ የስራ ዕድል እያገኘ መምጣቱ የተስተካከለ የኢኮኖሚ እድገት እንዳለ ጠቆሚ ነው። በእኛ አገር የኢኮኖሚ አቀንጭራ አሊያም የኢኮኖሚ ልምሻ የገባው በህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት፣ በ1983 በትረ-ሥልጣኑን እንደተቆጣጠሩ በኤርትራ ይገኙ የነበሩትን

ኢንዱስትሪ ዘርፍ፣የነበሩ ብዙ ፋብሪካዎች ከኢትዮጵያ ፋብሪካዎች በተገነጠሉ ግዜ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተቀጨ።

ከዚህ ግዜ በኃላ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ ንፅፅር 1:2፣ 1:3 1:4 በላይ እየሆነ የአገልግሎት ዘርፍ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፅኦ እያደረገና የሥራ እድልም አስተዋፅም ከፍተኛ እየሆነ ሄደ። በዚህም ምክንያት በአንድ አገር፣ያለ ኢንዱስትሪ እድገት መዋቅራዊ ለውጥ/መሠረታዊ ለውጥ ይመጣል ብሎ መመኘት ዘበት ነው። ሌሎች አገራቶች ያደጉት ከግብርና፣ወደ ኢንዱስትሪ ብሎም ወደ አገልግሎት ዘርፍ በተደረገ መዋቅራዊና መሠረታዊ ለውጥ (Structural Transformation) ዝግመታዊ ለውጥ አማካኝነት ነው።

የህንድ ኢኮኖሚ የምጣኔ ኃብት የተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ለአማካይ ዓመታዊ ብሄራዊ ምርት (ጂዲፒ) የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ደግሞ የግብርና ዘርፍ 17 በመቶ፣የኢንዱስትሪው ዘርፍ 29፣7 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፍ 45 በመቶ (በ2015 እኤአ ግምት መሠረት) ነበር። የዘርፎቹ የሥራ ዕድል ፈጠራ ግብርና 49በመቶ፣ኢንዱስትሪ 20 በመቶ፣ አገልግሎት 31 በመቶ (በ2012 እኤአ ግምት መሠረት)ነበር።

የእንግሊዝ ኢኮኖሚ የምጣኔ ኃብት የተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ለአማካይ ዓመታዊ ብሄራዊ ምርት (ጂዲፒ) የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ደግሞ የግብርና ዘርፍ 0.6 በመቶ፣የግንባታ ዘርፍ 6.4 በመቶ፣ የምርት ዘርፍ 14.6 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፍ 78.4 በመቶ (በ2014 እኤአ ግምት መሠረት)ነበር።

ዛሬም የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛውን የሰው ኃይል በመቅጠር፣ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ትልቁን ድርሻና አስተዋፆኦ በማድረግና በውጪ ንግድ ከፍተኛውን ገቢ በማስገኘት ግዙፍ ሚና ይጫወታል።

በአንፃሩ የኢንደስትሪው ዘርፍ፣ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት አስተዋፅኦው በ1991 እኤአ 9 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014እኤአ 14 በመቶ የቀጨጨ እድገት አሳይቶል። በሌላ በኩል የአገልግሎቱ ዘርፍ ለጂዲፒ ድርሻ በ1991 እኤአ 34.59 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014እኤአ 46 በመቶ እድገት አስመዝግቦል። በኢንደስትሪው ዘርፍ ዝቅተኛ ምርታማነት፣ ገቢ፣ የቴክኖሎጅ ሽግግርና በምርት ላይ ተጨማሪ እሴት አለመታከል እንዲሁም ምርት ወደ ውጪ ንግድ አለማቅረብ ታክሎበትና በአለም አቀፍ የገበያ ውድድር ላይ ብቃትና የአንድ ሸቀጥ የማምረቻ ዋጋ ከፍተኛ መሆን የኢንደስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት ገድቦታል። በኢትዩጵያ የኢንደስትሪው ዘርፍ ላይ የተሰማራ የሠራተኛ ቁጥርና የከተማዎች መስፋፋት በተፋጠነ ሁኔታ ማደግ አለበት፣በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወትና ተጨባጭ መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ከተፈለገ።

{1} የግብርናው ዘርፍ በ2007/08 ዓ/ም 36.4 በመቶ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) 69 ቢሊዮን ዶላር ድርሻው መቀነስ ምክንያት ማለት ከግብርናው ዘርፍ የተገኘው 25.1 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን፣ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ 11.5 ቢሊዮን ዶላርና ከአገልግሎት ዘርፍ 32.4 ቢሊዮን ዶላር ድርሻ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) አስተዎፅኦ አድርገዋል። በጣም ለማመን የሚያስቸግር መረጃ ነው። የአገልግሎት ዘርፍ 32.4 ቢሊዮን ዶላር ለጂዲፒው ድርሻ አለው ነው የሚሉን።

‹‹የዓለም የገንዘብ ድርጅት ሪፖርት በ2015 እኤአ መሠረት የግብርናው ዘርፍ 43 በመቶ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ እንዳለው፣ 80 በመቶ የሚሆነውን የሥራ ዕድል እንደፈጠረና ለሃገሪቱ የውጪ ንግድ 90 በመቶ ምርት በመላክ አንድ ሦስተኛውን የውጪ ንግድ ገቢ በማስገኘት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በጥናታቸው አረጋግጠዋል።››

"A very significant role for agriculture, given its share in GDP (43 percent), its role for employment (almost 80 percent of the workforce), and its importance for exports (accounting for 90 percent of goods exports, and a third of total exports)"

November 2015, The Federal Democratic Republic of Ethiopia

IMF Country Report No. 15/326, E-mail: publications@imf.org, Web: http://www.imf.org

በኢትዮጵያ የሰው ኃይል (Labour force) 37.9 ሚሊዩን በግብርናው ዘርፍ የተሰማራው ከ32.2 ሚሊዩን ህዝብ 84.9 በመቶ የስራ ዕድል የተፈጠረው በግብርናው ዘርፍ ነው።የውጪ ምንዛሪም ሃገሪቱ በአመዛኙ የምታገኘው 75 በመቶ ከግብርናው ዘርፍ ነው። የሃገሪቱ ህዝብ ከርሃብና ከድርቅ ተላቆ አያውቅም። አገሪቱ በምግብ እራሶን ችላ አታውቅም። የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስርዓታችን በኩረጃና በቅጂ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ህወሓት መንግስት ህዝቡን ከድህነት ቀንበር ሊያላቅቁት አልቻሉም። ሃገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በማውጣት ገበሬውን ያሳተፈና ተጠቃሚ የሚደርግ የባለቤትነት ስሜት የሚያጎናፅፈውና መብት የሚሠጠው ልማት መተግበር አለበት። የመሬት ቅርምት መቆም አለበት። ዴሞክራሲያዊና ስብዓዊ መብቶቹ መጠበቅ አለባቸው። በኢህአዴግ መቃብር ላይ!!!

## {2} የኢንዱስትሪ ዘርፍ

የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከ7 በመቶ ወደ 16.6 በመቶ እድገት ማሳየቱ 11.5 ቢሊዩን ዶላር ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻ አስመዝግቦል። በኢንዱስትሪው ዘርፍ ለ1.9 ሚሊዩን ህዝብ የስራ ዕድል ፈጥሮል ማለትም 5.0 በመቶ ማለት ነው። ከግብርናው ዘርፍ ወደ ኢንደስትሪ ዘርፍ የተሸጋገረው ወይም ከገጠር ወደ ከተማ የተሸጋገረው ህዝብ ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው።

## {3} የአገልግሎት ዘርፍ

የአገልግሎት ዘርፍ ከ17.2 በመቶ ወደ 47.0 በመቶ እድገት ለጠቅላላ አማካይ የሀገር ውሰጥ ምርት ድርሻው እድገት ነው የሚያሳየው።የአገልልሎት ዘርፍ ለ3.8 ሚሊዩን ህዝብ ሥራ መፍጠሩ ይታመናል።
ከአገልግሎት ዘርፍ 32.4 ቢሊዩን ዶላር ድርሻ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) አስተዎፅኦ አድርገዋል። በጣም ለማመን የሚያስቸግር መረጃ ነው። የአገልግሎት ዘርፍ ዋና ዋናዎቹ፣ የኢትዩጵያ አየር መንገድ የአገልግሎት ገቢ፣ የቱሪዝም የአገልግሎት ገቢ፣ የኤሌትሪክ ኃይል አገልግሎት ሽያጪ ገቢ፣ከውጪ የተላከ የሃዋላ ገቢ ወዘተ 32.4 ቢሊዩን ዶላር ተገኘ ነው የሚሉት!!! በሬ ወለደ እንደማለት ይቆጠራል። በኢትጵያ ኢኮኖሚ ታሪክ የአገልግሎት ዘርፍ ይህን ያህል ቢሊዩን ዶላር አስመዝግቦ አይታወቅም።

- Ethiopia's economy is mostly based on agriculture, which accounts for 42.7 percent of GDP, 90 percent of foreign currency earnings and 80 percent employment, whereas industry, accounts for 12.3 percent of GDP, and services with 45 percent of GDP. The number of people engaged in paid employment very nearly doubled between 2006 and 2013 alone, and these figures are set to expand further in the near future (Zerihun et.al.2014; EIG, 2013). Around 80 percent of the population derives its livelihood directly or indirectly from agricultural production.
- The climate is a strong asset for activities like floriculture, an area in which the government is particularity keen to attract foreign direct investment. Various studies indicate that agricultural exports, mainly coffee, processed, and semi-processed hides and skins account for over 80 percent of all the export. Coffee alone account for over 64 percent of foreign exchange earnings (EIC, 2015; MoT, 2015).
- በ1994ዓ/ም እኢአ በኢትዩጵያ በተደረገው የህዝብ ቆጠራ፣ ጠቅላላ የህዝብ ቁጥር 52,932,117 ሚሊዩን ሲሆን የከተማ ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር 7,176,230 ማለትም 13.6 መቶኛ ነበር። እንዲሁም የገጠር ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር 45,755,887 ሲሆን ማለትም 86.4 በመቶኛ ነበር።

- በ2010 እኤአ(2003ዓ/ም) በኢትዩጵያ የህዝብ ቁጥር፣ ጠቅላላ የህዝብ ቁጥር 85,000,000 ሚሊዩን ሲሆን የከተማ ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር 14,960,000 ማለትም 17.6 መቶኛ ነበር፡፡ እንዲሁም የገጠር ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር 70,040,000 ሲሆን ማለትም 82.4 በመቶኛ ነበር፡፡

| ዓመት | ጠቅላላ የህዝብ ቁጥር | ከተማ | በመቶ | ገጠር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1994 | 52,932,117 | 7,176,230 | 13.6 | 45,755,887 | 86.4 |
| 2003 | 85,000,000 | 14,960,000 | 17.6 | 70,040,000 | 82.4 |

- በኢትዩጵያ የከተማ ህዝብ 17.6 በመቶ ሲሆን በአፍሪካ 40.0 በመቶ፣ በሌሎች ታዳጊ አገራቶች 44.8 በመቶ እንዲሁም በአደጉ አገራቶች 77.7 በመቶ የከተማ ውስጥ ንዎሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የግብርናው ዘርፍ ከ44.4 በመቶ 36.4 በመቶ ከብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት ድርሻውን ቢቀንስም ወደ ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፎች የተሸጋገረውን የህዝብ ቁጥር ጥቂት እንደሆነ አሊያም ከገጠር ወደ ከተማ አዲስ የሥራ እድል ያገኙ ጥቂት ዜጎችን ብቻ እንደሆኖ ያሳያል፡፡ በብዙ የአፍሪካ አገራቶች 40 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የሚኖረው በከተሞች ውስጥ መሆኑን ማስረጃው ያሳያል፡፡
- በ2010 እኤአ በኢትዩጵያ የሥነ-ህዝብ አጠቃላይ እድገት በዓመት 2.6 በመቶ ሲሆን፣ በአፍሪካ 2.3 በመቶ፣ በታዳጊ አገራቶች 1.3 በመቶ እንዲሁም በሌሎች በታዳጊ አገራቶች 0.7 በመቶ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

- በ2010 እኤአ በኢትዩጵያ የከተማ ነዋሪዎች የህዝብ እድገት ንፅፅር በዓመት 4.4 በመቶ ሲሆን፣ በአፍሪካ 3.3 በመቶ፣ በሌሎች ታዳጊ አገራቶች 2.4 በመቶ እንዲሁም በአደገት አገራቶች 1.0 በመቶ

| Demographic Indicators | Ethiopia | Africa | Developing countries | Developed countries |
|---|---|---|---|---|
| Total Population (millions) 2010 | 85.0 | 1,031.5 | 5,629 | 1,069 |
| Urban Population (% of Total) 2010 | 17.6 | 40.0 | 44.8 | 77.7 |
| Population Growth Rate - Total (%) 2010 | 2.6 | 2.3 | 1.3 | 0.7 |
| Population Growth Rate - Urban (%) 2010 | 4.4 | 3.3 | 2.4 | 1.0 |

Sources : ADB Statistics Department Databases;

**የጥገኝነት ንፅፅር፣**Dependency Ratio

| ያታ | የዕድሜ ደረጃ | | | | የጥገኝነት ንፅፅር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0-14 | 15-64 | 65ና በላይ | አጠቃላይ ዕድሜ | ወጣት | ሽማግሌ | አጠቃላይ |
| ከተማና ገጠር | | | | | | | |
| በቁጥር | 24,132,982 | 27,301,784 | 1,697,487 | 53,132,253 | 88.4% | 6.2% | 94.6% |
| በመቶኛ | 45.4% | 51.4% | 3.2% | 100.0% | | | |
| ከተማ | | | | | | | |
| በቁጥር | 2,778,462 | 4,317,347 | 219,868 | 7,315,677 | 64.4% | 5.1% | 69.4% |
| በመቶኛ | 38.0% | 59.0% | 3.0% | 100.0% | | | |
| ገጠር | | | | | | | |
| በቁጥር | 21,354,520 | 22,984,437 | 1,477,619 | 45,816,576 | 92.9% | 6.4% | 99.3% |
| በመቶኛ | 46.6% | 50.2% | 3.2% | 100% | | | |

በኢትዩጵያ የጥገኝነት ንፅፅር በ2010 እኤአ 86.5 በመቶ በአፍሪካ ይህው 77.6 በታዳጊ አገራቶች 52.8 እንዲሁም በአደጉ አገራቶች 49.0 በመቶ ነበር፡፡ በኢትዩጵያ የጥገኝነት ንፅፅር በከተማ

ውስጥ 69.4 በመቶ ህዝብ የቤተሰብ ላይ ጥገኛ ሲሆን ማለትም፣ ለአቅም አዳምና ሄዋን ያልደረሱና ሽማግሌዎች ‹‹ለምግብ የደረሱ ፣ለስራ ያልደረሱ!!!›› ሲሆን 30.6 በመቶ አባወራና እማወራ እንጀራ አጉራሽ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ናቸው፡፡ በኢትዩጵያ ገጠር የሚኖሩ ህዝቦች 99.3 በመቶ ጥገኛ ሲሆኑ 0.7 በመቶ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ናቸው፡፡ የኢትዩጵያ የጥገኝነት ንፅፅር አሳዛኝ ሁኔታን ከአፍሪካ፣በሌሎች ታዳጊ አገራቶችና፣ ያአደጉ አገራቶች ጋር በማወዳደር ያለንበትን ደረጃ መገናዘብ ያሻል፡፡

Dependency Ratio (%) 2010 86.5 77.6 52.8 49,O
Sources : ADB Statistics Department Databases;

| ተ/ቁ | የኢኮኖሚ ዘርፍ | ዓ/ም 2003 | ዓ/ም 2008 | በኢኮኖሚ ዘርፉ የተሰማራ የሰው ኃይል በመቶኛ በ2007እኤአ ግምት **Labour force by occupation 2007** Estimate | በዘርፉ የተሰማራ የሰው ኃይል በሚሊዩን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና | 44.4% | 36.4% | 85% | 32.2 |
| 2 | ኢንዱስትሪ | 10.4% | 16.6% | 5% | 1.9 |
| 3 | አገልግሎት | 45.2% | 47.0% | 10% | 3.8 |

**Labour force** 37.9 million 2007 Estimate

የገጠርና የከተማ የሠራተኛ ኃይል ሽግሽግ ማለትም ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሠት ኢምንት መሆኑ የግብርናው ዘርፍ ለብሄራዊ አማካይ አመታዊ ምርት (ጂዲፒ) አስተዎፅኦ በቀነሰ ቁጥር፣ የተሰማራው የግብርና ሠራተኛ ቁጥር በጣም አነስተኛ መሆን ኢኮኖሚ ልምሻ እንጂ እድገትን አያመላክትም፡፡ ምክንያቱም አሁንም በምግብ ራሳችንን አልቻልንም፣ ከአስቸኮይ እርዳት ምፅዋት ከመለመን አልዳንም፡፡
በ2013 እኤአ የአለም ባንክ የዓለም እድገት ጠቆሚ 2013/ዩኤንዲፒ የሰው ኃይል ልማት ሪፖርትበ2013 መሠረት፣የኢትዩጵያ ህዝብ ብዛት 91.7 ሚሊዩን ሲገመት ከዚሁ ውስጥ 17.3 በመቶው ማለትም 15..9 ሚሊዩን ህዝብ የከተማ ውስጥ ኖሪዎች ሲሁኑ 82.7 በመቶው ደግሞ ማለትም 75.8 የገጠር ኑዋሪዎች ናቸው፡፡ በአፍሪካ አገራቶች 40 በመቶው የከተማ ንዋሪዎች ሲሆኑ 60 በመቶው የገጠር ንዋሪዎች ናቸው፡፡ ከገጠር ግብርናው ዘርፍ የተሰማራ የሠራተኛ ኃይል ወደ ከተማ ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፎች ለመቀጠር ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ሠራተኛ ህዝብ ቁጥር መጨመር ነበረበት፡፡

- Population  91.7 million, Urban population 17.3%, Rural population 82.7% (source: The World Bank, World Development Indicators 2013/ UNDP, Human Development Report 2013.)

በ2015 እኤአ ሲአይኤ ፋክት ቡክ ሪፖርት መሠረት፣የኢትዩጵያ ህዝብ ብዛት 99,465,819 ሚሊዩን ሲገመት ከዚሁ ውስጥ 17.3 በመቶው ማለትም 17.2 ሚሊዩን ህዝብ የከተማ ውስጥ ኖሪዎች ሲሁኑ 82.7 በመቶው ደግሞ ማለትም 82.2 ሚሊዩን የገጠር ኑዋሪዎች ናቸው፡፡

- Population  99,465,819, and expected to be 120 million in 2030 (CIA Fact book, August 2015)

## የብሄራዊ ባንክ ዓመታዊ ሪፖርት

የ2008ዓ/ም አማካይ ብሔራዊ ዓመታዊ ጠቅላላ ምርት ስምንት በመቶ ዕድገት እንዳሳየ በምርትና የገንዘብ የብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ይናገር ደሴ ገልፀዋል፡፡ ከዘጠኝ ወራቱ የእቅድና አፈፃፀም በመነሳት የ2008ዓ/ም የሃገሪቱ የውጪ ንግድ 2.86 ቢሊዩን ዶላር እንዲሁም የሃገሪቱ የገቢ ንግድ 22 ቢሊዩን ዶላር ሲደርስ የንግድ ሚዛን ጉድለቱ 19.14 ቢሊዩን ዶላር ይገመታል፡፡ በዚህም ምክንያት የ2008ዓ/ም የዕቅድና አፈፃፀም ንፅፅር ቁልቁል የወረደ መሆኑን ይተነበያል፡፡ የውጪ ንግድ ጉድለት የውጪ ምንዛሪ ሀብትን ስለሚቀንስ፣ የገቢና ወጪ ንግድ ሲሰላ የንግድ ሚዛን ጉድለቱ ከመቼውም ግዜ የበለጠ ሆኖል፡፡ በዚህም ምክንያት የውጭ ምንዛሪ ሀብትና የአገር ውስጥ ብድርሀብት ንፅፅር ሁኔታ በብር የውጭ ምንዛሪ መጣኝ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሳይታለም የተፈታ ነው ይላሉ የኢኮኖሚ ጠበብት፡፡ የአገሪቱ ቁልል የውጭ ዕዳ ክምችትም መጠመሩና የዕዳ የመክፈል አቅም ማጣት የተነሳ የዓለም ባንክ የኢትዩጵያን ብር ምንዛሪን እንዲቀንስ መጠየቃቸው የአገሪቱ

ኢኮኖሚ ውድቀትን ያሳያል። ለዚህም ይመስላል እርግጠኛ አማካይ ዓመታዊ ጠቅላላ የሃገር ውስጥ ምርት (Real GDP) እና ምስለ አማካይ ዓመታዊ ጠቅላላ የሃገር ውስጥ ምርት (Nominal GDP) በምርትና የገንዘብ ከመግለፅ ተቆጥበው የ2008ዓ/ም የዕቅድና አፈፃፀም በስምንት በመቶ እድገት በመግለፅ ብቻ ሸውደዋል።

## {II} በ2008ዓ/ም በጀት ዓመት ከውጪ ንግድ ዘርፍ በአፈፃፀም 2.86 ቢሊዩን ዶላር ሆነ።

‹‹የውጪ ንግድ መዳከም በፋይናንስ ዘርፍ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው››

‹‹በ2008ዓ/ም በጀት ዓመትም በአገር አቀፍ ደረጃ በውጪ ንግድ ላይ የታየው አፈፃፀም ደካማ እንደነበር የገለፁት አቶ ታዬ ዲበኩሉ፣በአገር አቀፍ ደረጃ 4.22 ቢሊዩን ዶላር ገቢ ከውጪ ንግድ ዘርፍ ለመግኘት ታቅዶ በአፈፃፀም የተመዘገበው ግን 2.86 ቢሊዩን ዶላር ብቻ እንደነበረ የህብረት ባንክ ፕሬዜዳንት አስታውቀዋል። በወቅቱ በአገር ደረጃ ለውጪ ንግድ ከቀረቡ የምርት አይነቶች መካከል ከዕቅድ በላይ አፈፃፀም የተመዘገበው በሻይ ቅጠል ምርት ብቻ ሲሆን፣ በተቀሩት ሁሉም ዓይነት ሸቀጦች የታየው አፈፃፀም ከዕቅድ በታች ሆኖ መመዝገቡ በዘርፉ ላይ ያለውን ክፍተት ያሳያል ብለዋል። በዘርፉ እየታ ካሉት ዋናዋና ችግሮች ውስጥ ለውጪ ንግድ ሸቀጦች ያለው ኣለም አቀፍ የገበያ ፍላጎት መቀዛቀዝ፣የምርት ግብዓትና የጥራት ሁኔታ መጎደል፣የቴክኖሎጅ አቅም ውስንነት ይገኙበታል። ከዚህም ባሻገር ብቁና የሠለጠነ የሰው ኃይል እንደልብ ያለመገኘቱ፣ በዘርፉ የሚታየው ህገወጥ ንግድ ሊገታ አለመቻሉ የውጪ ንግዱን እየፈተኑት ከሚገኙ ችግሮች መካከል በግንባር ቀደምትነት እንደሚጠቀሱ አስታውሰዋል። ››

**የውጪ ንግድ ገቢ ከ2006 እስከ 2015 እኤአ**

| | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2015 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የውጪ ንግድ ገቢ (Export Earnings) | 1,000.3 | 1,185.1 | 1,465.7 | 1,447.9 | 2,003.1 | 2,747.1 | 3,152.7 | 3,075.2 | 2.860.0 |

Source: Ethiopian Revenue and Customs Authority የውጪ ንግድ ገቢ(Export Earnings)

በ2015 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ 2,860,000 ቢሊዩን ዶላር የሚያወጣ የአገር ውስጥ ምርት ወደ ውጭ ሃገራት ተልከል። በአንፃሩም 22,000,000 ቢሊዩን ዶላር የሚያወጣ የውጭ ሃገር ምርት ወደ ሃገራችን ገብቶል። በዚህም የተነሳ -19,140,000 ቢሊዩን ዶላር የንግድ ኪሳራ (Trade deficit) ተመዝግቦል።

Export Partners፡ China 13 percent, Saudi Arabia 8.3 percent, Germany 8.3 percent, US 8.1percent

Import Partners፡ China 15.3 percent, Saudi Arabia 8.1 percent, India 7.2 percent and US 5.6 percent and Belgium 7.1 percent Source: CIA Fact book, August 2015

## {III} *በኢትዮጵያ ከውጭ የተላከ ገንዘብ በ2008 ዓ/ም 4 ቢሊዩን ዶላር ተመዘገበ*

*በኦሮሚያና በአማራው ክልሎች በተቀሰቀሰው ህዝባዊ እንቢተኝነትና ተጋድሎ ከባህር ማዶ ሃገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሰደተኛች በቤተሰቦቻቸውና በዜጎች ላይ ለደረሰ የህይወት መሰዋትነት፣ እስራት፣ስደትና ንብረት መውደም ያደረጉት ድጋፍ፣ ከውጭ የተላከ የገንዘብ 4 ቢሊዩን ዶላር መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦል። ይህም የውጭ ሃዋላ አገሪቱ ከውጪ ንግድ ካገኘችው 2.86 ሚሊዩን ዶላር 71.5 በመቶ ብልጫ እንዳለው ተስተውሎል። የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት በኢኮኖሚ እንዲያንሰራራና በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲጠናከር አድርጎታል። በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ይሄን የመንግስት የገቢ ምንጭ እስካላደረቁ ድረስና በሌላ መንገድ ገንዘብ መላክ ዘዴ እስካልተጠቀሙ ድረስ ህዝባዊውን ትግል መታፈኑ አይቀሬ ሆኖል። ስለዚህ የውጭ ሃዋላ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ተለያዩ ዘዴዎችን በመፍጠር የመንግስትን የውጪ ምንዛሪ ገቢ ለማስቀረት መምክርና ዘዴዎች በመፍጠር ወገኖቻቸውን መርዳት ይጠበቅባቸዋል እንላለን።* *2.1.12 Export revenues have more than doubled since 2004, reaching US$ 2 billion in 2010. The share of non-traditional exports, notably flowers, gold, meat and leather products increased to 74.6% in 2010 from 60%. Over the same period imports, especially for capital goods, grew rapidly (on average by about 27.4% per annum). FDI and remittances have also witnessed strong growth. Within a period of six years, FDI increased eightfold to reach US$ 950 million in 2010.*

*Remittances grew, on average, by 34% per annum to reach US$ 2.2 billion. However, the current account deficits remained high, at an average of 6% of GDP, due to the fact that Ethiopia is an importer of oil and capital goods.*

*የኢትጵያ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ንፅፅር መክሸፍን ለኀሊና ፍርድ*

*Box 2: Main Targets of GTP (2011-2015)*
* Reduce poverty from 29.2% to 22.2%;*
* 11% real GDP growth rate per annum (base case scenario); and  15% (high case scenario);*
* Increase exports from 10.5% to 31.2% of GDP;*
* Increase road density from 44.5 km/1000km2 to 123.7;*
* Increase power generation capacity from 2000 MW to 10,000 MW;*
* Raise industry's contribution to GDP from 13% to 18.7%.*
*Source: MoFED.  Macroeconomic Policy and Management Directorate*

*የኢትዩጵያ የቤት ሠራተኞች ዜጎች ስደት* *Migrant Domestic Workers*

*የሰራተኛና ማህበራዊ ኑሮ ጉዳይ ሚኒስቴር (* MoLSA Ministry of Labour and Social Affairs*) በተገኘው መረጃ መሠረት በኢትዩጵያ በአምስት ክልሎች ወደ ውጭ አገራቶች የፈለሱ የቤት ሠራተኞች ብዛት በአራት ዓመት ከ8 ወራቶች ውስጥ ያለውን ህጋዊ የቤት ሠራተኞ ስደተኞችን በግል ሠራተኛ ቀጣሪ ኤጀንሲዎች(* PEAs Private Employment Agencies) *አመቻችነትና የሰራተኛና ማህበራዊ ኑሮ ጉዳይ ሚኒስቴር አፅዳቂነት የተላኩ ኢትዩጵያዊያን ናቸው፡፡*

*Table 1:- Number of migrant domestic workers from five regions for 4 years and 8 months time*

| *Region* | *2008 Sept.- 2009 August* | *2009Sept.- 2010 August* | *2010Sept.- 2011 August* | *2011Sept.- 2012June* | *2012 July- 2013 February* | *Total* |
|---|---|---|---|---|---|---|
| *Tigray* | *949* | *573* | *1,582* | *8,592* | *4,966* | *16,662* |
| *Amhara* | *3,551* | *1,952* | *10,769* | *62,836* | *33,831* | *112,939* |
| *Oromia* | *3,600* | *2,757* | *10,430* | *64,431* | *39,185* | *120,403* |
| *SNNP* | *1,981* | *1,300* | *4,547* | *23,392* | *13,813* | *45,033* |
| *Addis Ababa* | *7,251* | *6,860* | *11,813* | *26,774* | *11,472* | *64,170* |
| *Total* | *17,332* | *13,442* | *39,141* | *186,025* | *103,267* | *359,207* |

*በግል ሠራተኛ ቀጣሪ ኤጀንሲዎች የሠራተኛ ቅጥር ፎርም በማስሞላት፣ከኤጀንሲው ጋር የሚላኩት የቤት ሠራተኞች በመፈራረም፣  የቤት ሠራተኞች ወጪ በመሸፈን፣የቪዛ አገልግሎት ለሚሄዱበት አገር በመክፈል፣ደርሶ መልስ የዓየር ትኬት በመቁረጥ፣የመኖሪያ ፍቃድና የሥራ ፍቃድ ክፍያና ዋስትና ሽፋን (ኢንሽራንስ)በመግባትየመሳሰሉት ወጪዎች በኤጀንሲው ይሸፈናሉ፡፡ ቀጥሎ ያለው ሠንጠረዥ ከኢትዩጵያ ወደ አረብ አገራቶች የፈለሱ የቤት ሠራተኞች ብዛት ያሳያል በዚህም መሰረት ሳውዲ አረቢያ 76 በመቶ እጁን ሥትይዝ በመቀጠል ኩዌት 24 በመቶ የቤት ሠራተኛ እንደቀጠሩ ማስረጃው ያሣያል፡፡*

*Table 2:- The number of migrant domestic workers to the Gulf from September 2008 to February 2013*

| *Country* | *2008 Sept.- 2009 August* | *2009Sept.- 2010 August* | *2010Sept.- 2011 August* | *2011Sept.- 2012June* | *2012July- 2013 February* | *Total* |
|---|---|---|---|---|---|---|
| *Saudi Arabia* | *9,399* | *2,395* | *13,446* | *158,959* | *92,691* | *276890* |
| *Kuwait* | *6,976* | *10,837* | *25,457* | *28,476* | *11,440* | *83186* |
| *Dubai* | *113* | *142* | *510* | *321* | *0* | *1086* |
| *Others* | *905* | *19* | *115* | *175* | *59* | *1273* |
| *Total* | *17,393* | *13,393* | *39,528* | *187,931* | *104,190* | *362435* |

ኢትዩጵያ የሠራተኛ ስምምነት የፈረመችው ከኩዌት ጋር ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ሳውዲ አረቢያ በቀን 1500 የቤት ሠራተኞች በቀን የምትወስደው አገር የሠራተኛ ስምምነት ጥያቄን ውድቅ በማድረግ ለመፈረም አሻፈረኝ ብላ ቆይታለች፡፡ የዜጎች ሞት፣በአመዛኙ እራሳቸውን የማጥፋት ስበብ/ምክንያት፣የወሲብ ትንኮሳ፣ የሥነ-ልቦና ቀውስ፣ የአካል ጉዳት ስቃይ ለመከታተል፣ የኢንባሲዎችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድጋፍ ይጠይቃል፡፡

- The only country Ethiopia made a labour agreement with is Kuwait.  Whereas Saudi Arabia, that receives approximately 1500 domestic workers a day, avoids the question of having labour agreement with Ethiopia.
- There are many cases consulted at MoFA ( Ministry of Foreign Affairs) Consular Monitoring and Support Directorate office that indicate how the protection of the rights and safety of citizens in the Gulf region is not easy for the PEAs. Deaths of citizens, which most of them appropriated to be

suicidal cases, sexual, psychological and physical abuses require the Embassies' and MoFA's assistance.

**ኢትዩጵያ መንግስት ከሳውዲ ዓረብያ በግፍ የተባረሩ ከ150 ሽህ ዜጎች ሠራተናችና ስደተኞች እንደ አውሬ እየታደኑ መባረራቸው የቅርብ ግዜ ትዝታ ነበር። የህወሓት መንግሥት ከኩዌት፣ከኳታርና ከዩርዳኖስ መንግስታት ጋር የቤት ሠራተኞች ለመቅጠር የሁለትሽ የሥራ ሥምሪት ስምምነት ተፈራርመዋል። ለኢትዩጵያውያን ትልቅ ገበያ የሆኑትን ሳውዲ አረብያና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ አገራቶች የህወሓት መንግስት ሹማምንቶች በማማለልና በመደለል ላይ ይገኛሉ። የህወሓት የጦር አበጋዞች ልጆቻቸውን ወደ ባህር ማዶ አገራቶች ዶላር ከፍለው እያስተማሩ ሌሎቹን የእንጀራ ልጆች አረብ አገራት በቤት ሠራተኝነት ስራ አሰማርተው እነሱ ወደሃገር ቤት ለዘመዶቻቸው የሚልኩትን ዶላር የሃገሪቱ ትልቁ የውጭ ምንዛሪ ማግኛ፣ የሃዋላ ገቢ መሆኑን ስንቶቻችን እናውቃለን። ከውጪ የሚላክ ገንዘብ/ ሃዋላ ከሃገሪቱ ከምታገኘው የውጪ ንግድ መብለጡን ስንት ዲያስፖራ ያውቃል። ዲያስፖራው በእጁ ላይ ያለውን የገንዘብ መብት ቢጠቀም የህወሓት መንግስትን መቅጣት ይችል ነበር። በ2008 ዓ/ም በተነሳው ህዝባዊ እንቢተኛነትና ተጋድሎ የህወሓት መንግስት ከውድቀት ያገገመው ዲያስፖራው በላከው 4 ቢሊዩን ዶላር መሆኑን ስንቶቻችን እናውቃለን!!! ለዚህ ነው የሃሪቱን ኢኮኖሚ የማያውቅ ፖለቲካውንም አያውቅም የሚባለው።**

- The engagement of PEAs in illicit activities of recruiting rural women and girls through illegal brokers. The high competition among the 334 PEAs and between them and the illegal brokers according to an informant from MoLSA, drives the PEAs to perform their activities illegally since their objective is to maximize profit by recruiting as many job seekers as possible. There are PEAs who comply with the provisions of the Employment Service Proclamation 632/2009 for the only reason of preserving their license from revocation rather than with the concern of protecting the rights of citizens. Quoted at Fernandez (2010) a Yemeni informant whose wife is the owner of a large and one of the oldest PEAs stated as follows;
  'I am in the business of exporting cattle from Ethiopia, while my wife exports women and let me tell you, it is easier to export cattle [because there are fewer government regulations to comply with]' This implies that if there are no regulations regarding the woman power supply, women would be exported like cattle without considering what they would be facing in their owners apartments.
- The inability of the government itself in making bi-lateral labour agreements with the receiving countries. According to the information obtained from MoFA Consular Monitoring and support Directorat's share of domestic workers from Ethiopia i.e. per cent, the Saudi Arabia government is not willing to have a labour agreement. In addition, however it is stated in the Employment Exchange Proclamation that a labour attaché would be deployed in the countries to which Ethiopia supplies man power, this remains theoretical and the protection of citizens' mainly fall on the hands of PEAs. As described above, this study identifies the dilemmas that the rural Ethiopian women and girls face in countries to which they travel as domestic workers and it points out the different causes of disagreements between the domestic workers and their employers. In addition, the study also shows the obstacles to the effort of alleviating the problems of domestic workers in the Gulf.

  Source:The Vulnerability of Ethiopian Rural Women and Girls: The Case of Domestic Workers in Saudi Arabia and Kuwait/ Selamawit Bekele Woldemichael፡ At UPPSALA UNIVERSITY፣ June 2013

*የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግሥት ወደ ውጭ አገራቶች የቤት ሠራተኞች በብዛት በመላክ የውጪ ምንዛሪ ያግበሰብሳል። በኢትጵያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ሐዋላ ፍሰት ከመደበኛ (ህጋዊ) በሆነ መንገድ (መኒ ግርሃም፣ ዌስተርን ዩኒየን፣ድሃብሽን ወዘተ) እንዲሁም በአመዛኙ መደበኛ ባልሆነ (ህገወጥ) መንገድ የውጪ ምንዛሪ ውጭ ካሉ ዜጎቹ ይሰበስባል። ከ2008 እስከ 2013 እኤአ ከአረብ ሃገራት ከሚኖሩ 362435 የቤት ሠራተኞች፣ ኢትዩጵያዊያን ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ሃገር ቤት ላሉ ቤተሰቦችና ዘመዶች በመኒ ግርሃም፣ ዌስተርን ዩኒየን፣ድሃብሽን ወዘተ የላኩት ዶላር በኢትዩጵያ ባንኮች ገቢ ሆኖ ባንኮቹ ለዘመዶቻቸው በብር ይሠጡላቸዋል። የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግሥት የቤት ሠራተኞች ወደ አረብ አገራቶች በመላክ ሠራተኞቹ ለወላጆቻቸው ከውጭ የሚልኩት ዶላር (ሃዋላ) ትልቁ ገቢው ነው።*

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ታህሥስ 17 ቀን 2009ዓ/ም ‹‹ምጣኔ ሃብት ሲያድግ ስደት ለምን?›› በሚል ርዕስ በኢትዩጵያ በዓመት ከአንድ ሽህ ዜጎች መካከል ዘጠኙ ወደ ሌሎች አገራት ይሰደዳሉ፡፡ በ2015እኤአ በኢትዩጵያየሥነ-ህዝብ ቁጥር 99,465,819 ሚሊዩን ውስጥ 8,951,924ሚሊዩን ህዝብ በዓመት እንደሚሰደዱ ተገልፆል፡፡ በአይኦኤም መረጃ ሚያመለክተው ፣ በህጋዊና ህገወጥ መንገድ 9 ሚሊዩን ህዝብ በየኣመቱ ይሰደዳል፡፡ የምጣኔ ሃብት ባለሙያው ዶክተር ወልዳይ አምሃ እራሳቸው በጀርመን ሃገር ተሰደው ለስደተኞች የሚሰት ዳጎስ ለ ገንዘብ ተቀብለው ወደ ሃገር ቤት የገቡ ምሁር ናቸው፡፡ አሁን በስርአቱ ተጠቃሚ ሆነው ፎቅ ገንብተው ሆቴል ቤት ከፍተዋል፡፡ የኢትጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበርን ለህወሓት መንግስት አጎብዳጅ እንዲሆን ያደረጉ ካድሬ ናቸው ስለስደት ጥናት የሚያደርጉት፡፡ በኢትጵያ ውስጥ በየዓመቱ ሁለት ሚሊዩን ታዳጊዎች ወደ ወጣት የዕድሜ ክልል የገባሉ በዚህም የተነሳ 1.4 ሚሊዩን ወጣቶች አዲስ የስራ እድል ሊከፈትላቸው ይገባል ማለት ነው፡፡ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት አሳየች የምትባለው ሃገር የስደት ችግርን ለመፍታት አቅቶታል፡፡

- Population 99,465,819, and expected to be 120 million in 2030 (CIA Fact book, August 2015)

## በኢትዮጵያ ከውጭ የተላከ ገንዘብ/ የውጭ ሐዋላ ከ1995 እስከ 2015 እኤአ

በ1995 እኤአ ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ 27 ሚሊዩን ዶለር፣በ2000 እኤአ 53 ሚሊዩን ዶለር መድረሱን የብሄራዊ ባንክ ገዥ ይፋ አድርጎል፡፡ በግምት አንድ ሚሊዩን ከሚሆኑት ባህር ማዶ ሃገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሰደተኞች በ2012 እኤአ ከ1.2 እስከ 2.4 ቢሊዩን ዶለር ከውጭ ሐዋላ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገባ የብሄራዊ ባንክ ገልፆል፡፡ በ2006 እኢአ የዘጠኝ ወራት ሪፖርት መሠረት ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ ሁለት ቢሊዩን ዶለር ገደማ መድረሱን የብሄራዊ ባንክ ገዥ ይፋ አድርጎል፡፡
በዚህም መሠረት ከባህር ማዶ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሃገር ውስጥ የተላከ ገንዘብ የዓለም ባንክ ባወጣው መረጃ፣ ከሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው ዝቅተኛ ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ በ2001 እኤአ 18 ሚሊዩን ዶለር የነበረ ሲሆን ከፍተኛ 4 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር በ2015 እኤአ እድረት እንዳሳየ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገናቸውን በመርዳትና በማስተዳደር የሲሶ መንግስትነት ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛሉ ሰለዚህም በሀገራቸው ጉዳይ ከማንም በላይ ሊያገባቸውና ድምፃቸውም ሊሰማ ይገባቸዋል፡፡

Inward Remittances, Ethiopia 2000-2011

| Year | 2000 | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Remittances (USD Million) | 53 | 18 | 33 | 46 | 134 | 174 | 172 | 358 | 387 | 262 | 345 | 371 | 2.4 Billion | 3 Billion | 2 Billion | 4 Billion |
| % | | -15 | 183 | 139 | 291 | 130 | 99 | 208 | 108 | 68 | 132 | 107 | 647 | 125 | -67 | 200 |

Sources: Extracted from: The World Bank (2012) Remittances Data-inflow.

የውጭ ምንዛሪ ንዋየ-ኩብለላ ከሃገረ ኢትዩጵያ ወደ ባህር ማዶ ሃገራት (Illegal Ethiopian Capital Flight) በሚለው ጥናታዊ ፅሑፍ እንደተገለፀው ከሆነ፣6-Unrecorded remittances (ያልተመዘገቡ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ነዋሪዎች የተላከ የውጭ ሐዋላ 6.0 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር እንደነበረ ተዘግቦል፡፡ በአጠቃላይ ከ1970 እሰከ 2010 እኤአ በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 24,874.8 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ከኢትዮጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተቀምጦል፡፡ከ1970 እስከ 2010 እኤአ ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ ሸቀጦች በዝቅተኛ ዋጋ ደረሰኝ የተገዙ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ በቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር

1) አጠቃላይ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታል (Total capital flight) 24.9 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)፣
2) ያልተስተካከል‹ቀሪ›ሂሳብ (Unadjusted ‘residual’ measure ) 25.9 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)፣
3) ወደ ውጭ ከተላኩ ሸቀጦች በዝቅተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተሸጡ (Export misinvoicing)
2.5 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)፣
4) ወደ ሃገር ውስጥ የገቡ ሸቀጦች በከፍተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተገዙ (Import misinvoicing )
-9.5 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)፣
5) አጠቃላይ ንግድ በዝቅተኛና በከፍተኛ የዋጋ ደረሰኝ የተሸጡና የተገዙ (Total trade misinvoicing )
-7.1 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)፣
6) ያልተመዘገቡ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ሃገር ቤት ላሉ ቤተሰቦችና ዘመዶች የተላኩ የገንዘብ ድጎማዎች (Unrecorded remittances) 6.0 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር)

*የዓለም ባንክና የዓለም ዓቀፍ ገንዘብ ድርጅት  መረጃ ጥናት መሠረት በተለይም የውጭ ሐዋላ ፍሰት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከሃገር የሚወጣና የሚገባ ገንዘብ ልዩነት እንዳለው በመረጃ ተደግፎ  ተገልፆል። በዚህም ምክንያት በዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ሐዋላ ፍሰት በሚመለከት ተመዝግቦ የሚቀረበው ሪፖርት የተዛባ  መሆኑ በጥናት ይታወቃል። በኢትጵያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ሐዋላ ፍሰት ከመደበኛ(ህጋዊ) በሆነ መንገድና(መኒ ግርሃም፣ ዌስተርን ዩኒየን፣ድሃብሽን ወዘተ) እንዲሁም በአመዛኙ መደበኛ ባልሆነ (ህገወጥ) መንገድ እንደሚሰበሰብ ይታመናል።ከ1970 እስከ 2010 እኤአ ከውጭ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዬጵያዊያን ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ሃገር ቤት ላሉ ቤተሰቦችና ዘመዶች የተላከ ገንዘብ ወይም ያልተመዘገቡ የውጭ ሐዋላ (Unrecorded remittances) 6.0 ቢሊዩን ዩኤስኤ ዶለር ሲሆን፤ በአርባው አመታት ውስጥ በአማካኝ 150,000,000 ሚሊዩን ዩኤስኤ ዶለር በየዓመቱ  በህገወጥ መንገድ ተዘርፎል ማለት ይቻላል።ኢትዬጵያ ብሄራዊ ባንክ በ2010 እኤአ ብቻ መደበኛ ባልሆነ መንገድ 428 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ በግለሰቦች የተዘረፈ የውጭ ሐዋላ ንዋየ-ቅሽባ መፈፀሙን በግልፅ ተገልፆል። The NBE QuarterlyBulletin reports that of the above individual transfers, $428 million was “underground private transfers” (NBE 2010). ተብሎ ተገልፆል።*

*በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመነ አገዛዝ፣ በውጭ ሃገራት ልጆቻቸውን ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምሩ  የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣኖች፣ ነጋዴዎች፣ ወዘተ  መደበኛ ባልሆነ መንገድ በሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ በግለሰቦች የተዘረፈ የውጭ ሐዋላ ንዋየ-ቅሽባ በማድረግ ለልጆቻቸው የትምህርት ቤት ክፍያ ይፈፀማሉ። ይሄንን መረጃ ለማግኘት የነማን ልጆች ውጭ ይማራሉ፤ብዛታቸው ስንት ነው፣ የዩኒቨርሲቲው ክፍያ በአመት ስንት ዶለር ነው፣ወዘተ የመረጃ መጠይቆችን ግዜ ያወጣዋል።ዛሬ በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመነ አገዛዝ የደሃ ልጆች ከባህር ማዶ ሃገራት በመቶ ሽህ ዩኤስ ዶላር በመናጢ ደሃ አባቶቻቸው እየተከፈለላቸው ይማራሉ። እነዚህ የመንፈስና የህሊና ደሃ ሃገር መሪዎች ምርጥ አስተማሪ በጥሩ ክፍያ ሃገር ውስጥ አምጥቶ ማስተማር እየተቻለ የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሪና ሃብት በዚህ መልክ ይዘርፋሉ።ሌላው በህወሃት/ኢህአዴግ  ዘመን የስርአቱ ሹመኞች በውጭ ሃገራት ህክምና በማድረግ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በብዙ ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ የተዘረፈ የውጭ ሐዋላ ንዋየ-ቅሽባ በማድረግ የኢፈርትና የሜድሮክ ባንኮችና ኩባንያዎች ስውር የውጭ ሃገር የባንክ አካውንት በመክፈት ሹመኞች በታመሙ ግዜ ከነጠባቂ ወርዲያዋቻቸው ወደ ባህር ማዶ ሆስፒታሎች በመሄድ ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ።*

*ለማጠቃለያ በተባበሩት መንግስታት የሠላም አስከባሪ በመሆን ከሚያገለግለው የኢትዩጵያ ሠራዊት የደሃው የገበሬ ልጆች ያፈራቸው፤ በውጭ ምንዛሪ የሚገኙትን የወር ደሞዝ ክፍያ፤ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በሚሊዩን ዩኤስ ዶላር በህቡዕ በህወሃት/ኢህአዴግ ሹማምንት፤ የጦር አበጋዞች ‹ጀነራል መኮንኖች› እየተዘረፈ ለሠራዊቱ አባሎች በብር በመክፈል ዶለሩን ይዘርፋሉ በሠራዊቱ ደም ይነግዳሉ። ሹማምንቱ ባግበሰበሱት የውጭ ሐዋላ የዶላር ንዋየ-ቅሽባ፣ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ይገነባሉ።የኢትዬጵያ ብሄራዊ ባንክ ይሄ ሁሉ መረጃ እንዳለውና ወደፊት ግዜ የሰጠውና ሃገሬ ያለ ዜጋ እንደሚያጋልጠው ሳይታለም የተፈታ ነው። ከባህር ማዶ ከሚኖሩ ኢትዬጵያውያን የታላቁ ህዳሴ የቦንድ ሽያጭ በማምከን ድጋፋቸውን ነስተዋል። ኢትዬጵያውያኑ ሃገራቸውን በእውቀትና በገንዘብ እንዲያግዙ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መብትን ማክበር፣ ነፃ ምርጫ፣ነፃ ኢኮኖሚ የመሳሰሉትን ህዝባዊ ጥያቄዎች፣ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት ያሞላል ብሎ መጠበቅ የህልም እንጀራ በመሆኑ ውጭ የሚኖሩ ዜጎችን ድጋፍ ማግኘት አይቻለውም።*

ህዝባዊ እንቢተኝነት፣ በኦሮሚያ ክልል ለአንድ ዓመት በቆየውና በአማራው ክልል ደግሞ በ2008 ዓ/ም መጨረሻ ወራት ተከስቶ በነበረው ተቃውሞ በርካታ ህይወት ማለፉ ይታወቃል። በተጨማሪም በርካታ ኢንቨስትመንቶች፣ የግለሰብ ንብረቶችና የህዝብ የልማት ተቆሞች ላይ 202 ሚሊዩን ብር የሚገመት መጠነ ስፊ ውድመት አጋጥሞ እንደነበር መንግሥት ተቃዋሚዎቹን አስሮ ፍርድ ቤት አቅርቦል። መንግሥት ያመነውን  በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ምንም ጉዳት አላደረሰም ማለት ከአንድ የኢኮኖሚ ምሁር ሊያውም የብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ይናገር ደሴ አይጠበቅም።  የደረሰውን የኢኮኖሚ ውድመት የኢትዩጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዩጵያ ንግድ ባንክና የኢትዩጵያ መድን ድርጅት ለማጥናት የባለሙያዎች ኮሜቴ መቆቆሙ ለምን ይሆን? የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች ከሃገር መውጣታቸው ለምን ይሆን?

## {IV} የውጭ ዕዳ ክፍያ

በ2007 እኢአ የኢትዬጵያ የፌዴራል መንግስት በጀት 178.6 ቢሊዩን ብር ሆኖ በፓርላማ እንደፀደቀ ሲገለፅ ከዚህም ውስጥ የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ 8.2 ቢሊዩን ብር እንደሆነ ተገልፆል።ኢትዩጵያ ዕዳውን ለመክፈል በዓመት 8.2 ቢሊዩን ብር እየከፈለችና ሌላ ገንዘብ ሳትበደር እዳዋን ለመጨረስ ከ45 ዓመታት እስከ 68 አመታት ይፈጅባታል።

በ2008 እኢአ የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት ባጀት 223.3 ቢሊዮን ብር ከዚህም ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ከሃገሪቱ ባጀት ትልቁን ድርሻ የያዘው፣ የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ 11.903 ቢሊዮን ብር እንደሆነና  ተገልፆል። የውጪ እዳ ክፍያው ከ2007ዓ/ም በጀት  በ3,703,000,000 ቢሊዮን ብር ከፍ እንዳለ የአሃዙ ስሌት ያሳያል።

በ2009 እኢአ 274.3 ቢሊዮን ብር በጀት ቀርቦ ከዚህ ውስጥ 13.9 ሚሊዮን ብር የተያዘው ለውጭ ዕዳ ክፍያ መሆኑ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት በጀትና የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ

| ዓመት(ኢትዩጵየ አቆጣጠር) | መንግስት በጀት | የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ | ዕዳ የበጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 178.6 ቢሊዩን ብር | 8.2 ቢሊዩን ብር | 4.6 |
| 2008 | 223.3 ቢሊዩን ብር | 11.903 ቢሊዩን ብር | 5.3 |
| 2009 | 274.3 ቢሊዩን ብር | 13.9 ሚሊዩን ብር | 5.1 |

የኢትዮጵያ የውጪ ብድር ክምችት ከብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት ድርሻ በ2011 እኤአ 19.9 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014 እኤአ 27 በመቶ ነበር። የመንግሥታዊ ልማት ዘርፎች ብድር ከብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት ድርሻ በ2011እኤአ 20.9 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014 እኤአ 42.0 በመቶ ሆኖል። በ2016/17 እኤአ የህወሓት መንግስትና ብሄራዊ ባንክ ባለሞሎች የሃገሪቱን ልትወጣ በማትችለው የውጪ ብድር ክምችት ከተው ኢኮኖሚውን አዘቅት እንደሚከቱት አጥኝዎች ተንብየዋል። ለዚህም ግልፅ ማሸረጃ የ2009 ዓ/ም የመጀመሪያና ሁለተኛ በጀት ዓመት እቅድና አፈጻጸም፣ በተለይ የውጪ ንግድ ገቢ ማሽቆልቆል፣ የውጪ ብድር መክፈል አቅም መሽመመድና የውጪ ምንዛሪ እጥረት በቀጣይነት ይከሰታል። ቀጥሎ ያሉትን መረጃዎች ያንብቡት።

| Year | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| External Debt(%of GDP) | 19.9 | 22.1 | 22.6 | 27.0 | | |
| Public Debt (%Of GDP) | 20.9 | 21.6 | 22.3 | 42.0 | | |

External Debt (%of GDP) 2011(19.9),2012(22.1),2013(22.6)2014(27.0),2015(-)
PUBLIC DEBT(%OF GDP)2011(20.9)2012(21.6)2013(22.3)

Ethiopia's large-scale public investment in infrastructure has been financed by significant borrowing, which has resulted in higher public debt. Ethiopia reached the completion point under the Heavily Indebted Poor Countries (HIPC) Initiative in 2004 and benefited from debt relief under the Multilateral Debt Relief Initiative (MDRI) in 2006.1) Public and publicly guaranteed (PPG) external debt 2) fell in the years that followed, reaching a low of 22.1 percent of GDP in 2012. 3) It rose to 27.0 percent of GDP by 2014 (and total public debt was 42 percent of GDP)

- ለማጠቃለል የኢትዮጵያ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) አነስተኛ መሆን ምክንያት የሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት፣ በተቆለለ የውጭ ብድር ክምችትና የእዳ ክፍያ ምክንያት በረጅም ግዜያት ውስጥ እንደሚናጋና እንደሚጎዳ ያስገነዝባል።
- የኢትዮጵያ የውጭ ብድር በ1975 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 343.7 ሚሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 14% እጅ ይይዝ ነበር። በ1991 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 9.1 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 214% እጅ ይይዝ ነበር። በጁን 30 1999 ይሄ አሃዝ 10.2 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር ከፍ ብሎል።በ2011እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 7.102 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 23.5% እጅ ይይዝ ነበር። 2012እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 12 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) --% እጅ ይይዝ ነበር። 2013እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 16.11 ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት($46) ቢሊዮን ዩኤስ ዶለር (GDP) 35% እጅ ይይዝ ነበር።

## ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም!!!

የገንዘብ የብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ይናገር ደሴ የ2008ዓ/ም አማካይ ብሔራዊ ዓመታዊ ጠቅላላ ምርት ስምንት በመቶ ዕድገት እንዳሳየ ገልፀዋል።በ2008 ዓ/ም መጨረሻ ከውጪ ንግድ ይገኛል

ተብሎ የታቀደው ግብ 5.01 ቢሊዩን ዶላር ሲሆን፣የበጀት አመቱ ሊጠናቀቅ ሦስት ወራት የቀረው ሲሆን የውጪ ንግድ ገቢ እቅድ ከአፈፃፀሙ 50 በመቶ በታች እንደነበር ከራሳቸው መረጃ ምንጭ አጥኝዎች አገራግጠዋል። በተለያዩ ቦታዎች የሚገለፁት የተምታቱ መረጃዎች በመሆናቸው ልመዱት።

2008 የዘጠኝ ወራት የውጪ ንግድ ገቢ (ቢሊዩን ዶላር)

| ዘርፍ | ዕቅድ | አፈፃፀም | አፈፃፀሙ ከዕቅዱ በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| ከግብርና ምርቶች | 3.43 ቢሊዩን | 1.5 ቢሊዩን | 43.7 |
| ከማኑ-ፋክቸሪንግ | 1.06 ቢሊዩን | 258.58 ሚሊዩን | 24.4 |
| ማዕድን | 603 ሚሊዩን | 223.4 ሚሊዩን | 37.0 |
| ጠቅላላ | 5.093 ቢሊዩን | 1.981.98 ቢሊዩን | 38.9 |

የዘጠኝ ወራቱ አጠቃላይ የአገሪቱ የኤክስፖርት አፈፃፀም ቅናሽ ያሳየው ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር ብቻ አይደለም።ካለፈው 2007 በጀት ዓመት ጋር ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛ ነው።

- የ2008ዓ/ም የኢትዮጵያ የውጪ ንግድ፣ከዘርፉ 1.26 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ የተገኘው ገቢ ግን 722.4 ሚሊዩን ዶላር ነው። ስለዚህ የዘርፉ የውጪ ንግድ እንቅስቃሴ ከታቀደው ግብ ጋር ሲነፅፀር 70 በመቶ በመሆኑ በውጪ ንግዱ ላይ ከፍተኛ ዕድገት እንዲመዘገብ ጥረት ማድረግ ይገባል።
- የ2009ዓ/ም በጀት ዓመት የኢትዩጵያ የውጪ ንግድ፣የ2009 ዓ/ም በጀት አመት የውጪ ንግድ የሩብ ዓመት እቅድ 1.04 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር የነበረ ሲሆን አፈፃፀሙም 640.87 ሚሊዩን ዶላር ይህም 61.74 በመቶ ሆኖል። ይህ ሁኔታም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ8 በመቶ ቅናሽ አሳይቶል።

በ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪው ሩብ ዓመት አፈጻጸም ‹‹በአገሪቱ በሚገኙ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ውስጥ 24 የአበባና አትክልትና ፍራፍሬ ፕሮጀክቶችና 23 የኢንዱስትሪዎች ላይ ውድመት ደርሶል።በ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪው ሩብ ዓመት አፈጻጸም የሀገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በእጅጉ ተዳክሞል። ሀገሪቱ በሩብ ዓመቱ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆናም ከ3.5 ቢሊዩን የአሜሪካ ዶላር በላይ ካፒታል ያላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወደ ቀጣይ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንደሚገቡ መረጋገጡን ገልጸዋል። ባለሃብቶቹ 124 ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ 71 ከቻይና ሌሎች ከተለያዩ ሀገራቶች ተቀብሎ የማሳመን ስራ መሰራቱን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ ፍጹም አረጋ ገልጸዋል።›› ከዚህም በተጨማሪ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የመጀመሪው ሩብ ዓመት እቅድና አፈጻጸም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ተከስቶል። ሃገር ጎብኝ ቱሪስቶች በሃረጊቱ በታወጀው አስቸካይ ግዜ አዋጅ ምክንያት የሚያደርጉትን ጉብኝትና የሆቴል አገልግሎት ሰርዘዋል እንዲሁም በተያያዥ የኢትዩጵያ አየር መንገድም ገቢው አሽቆልቁሎል።

በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ውስጥ በተከሰተው ህዝባዊ አመፅ አንድም የቻይና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ላይ ጉዳት አልደረሰም፣ቻይና የኢትጵያ ቴሌኮምን ሙሉ በሙሉ ስለምትቆጣጠር መረጃው ቀድሞ የማግኘትና በኢህአዴግ ጦር ሠራዊት ፋብሪካቸውን ንብረት ማስጠበቅ በመቻላቸው ነው። *የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት ከስልጣን ሊወገድ የሚችለው የቻይና መንግስት ድጋፍና አጋርነት ሲወገድ ብቻ እንደሆነ መወቅ ያስፈልጋል።* የቻይና መንግስት የራሳቸውን ቀይ ሠራዊት በኢትጵያ በማስፈር ህወሓት መንግስትን እስከመታደግ ቃል ኪዳን አላቸው። ህወሓት ከቻይና ልማታዊ መንግስት የፖለቲካና ኢኮኖሚ አስተዳደርን ተውሶል፣ መሬት የመንግስት መሆኑን የሚደነግግ ፖሊሲ የጋራቸው ነው፣ የአንድ ፓርቲ አገዛዝና ፀረ-ዴሞክራቲክ መብቶች አቀም፣ የሰብአዊ መብቶች አለማክበር፣ የፕሬስ ነፃነትን ማፈንና ጋዜጠኞችን የማሰር ወዘተ፣የፍትህ ዕጦት፣ ኢንተርኔት መረቦችን፣ የተለያዩ ድረ-ገፆችን የመዝጋት፣ ሶሻል ሚዲያዎችን የመዝጋት የጋራ ፖሊሲዎቻቸው እንደሆኑ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

{5} የሀገር ቤት የኢትዩጵያ ኢኮኖሚ ዜና ሐተታ፣በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ጠበብት ጥናታዊ መረጃ መሠረት የኢትዩጵያ ኢኮኖሚ ከ2008 እስከ 2009 ዓ/ም እንደ ኢትዩጵያ አቆጣጠር ጀምሮ ምጣኔ ኃብቱ በከፍተኛ ውድቀት ላይ እንደሚገኝ ቀጥሎ እንደሚከተለው በማስረጃ ይቀርባል።

{5.1} የ2008ዓ/ም የኢትዩጵያ የውጪ ንግድ፣ ‹‹የዘርፉ የውጪ ንግድ መጠን ማሳዳግ እንደሚያስፈልገው ተገለፀ›› በሚል ርዕስ የንግድ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ አሰድ ዚያድ እንደገለፁት

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የመጀመሪያው ዓመት (2008ዓ/ም) ከዘርፉ 1 ነጥብ 26 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ የተገኘው ገቢ ግን 722 ነጥብ 4 ሚሊዩን ዶላር ነው፡፡ስለዚህ የዘርፉ የውጪ ንግድ እንቅስቃሴ ከታቀደው ግብ ጋር ሲነፅፀር አነስተኛ በመሆኑ በውጪ ንግዱ ላይ ከፍተኛ ዕድገት እንዲመዘገብ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡

የ2009 ዓ/ም በጀት ዓመት የኢትዩጵያ የውጪ ንግድ፣‹‹አሁንም ከፍተኛ ትኩረት የሚሻው የውጪ ንግድ›› የሚኒስትሩ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዩች ፅህፈት ቤት ተወካይ አቶ ሽመልስ አረጋ፣ የ2009 ዓ/ም በጀት አመት የውጪ ንግድ የሩብ ዓመት እቅድ 1.04 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር የነበረ ሲሆን አፈፃፀሙም 640.87 ሚሊዩን ዶላር ይህም 61.74 በመቶ ሆኖል፡፡ ይህ ሁኔታም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ8 በመቶ ቅናሽ አሳይቶል፡፡

{5.2} የ2008ዓ/ም የኢትዩጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ገቢ፣‹‹የቱሪዝም ዘርፍ የዚህ ዓመት የገቢ ዕቅድ በተከሰተው ሁከት ሰበብ መከለሱን ታወቀ››በሚል ርዕስ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ገዛህኝ አባተ፣ በበጀት ዓመቱ ከሃምሌ 2008 ዓ/ም ጀምሮ በነበሩት ሦስት ወራት ውስጥ የቱሪዝም ዘርፍ ያስመዘገበው ገቢ ከ872.5 ሚሊዩን ዶላር እንደሆነና ከ233 ሽህ ጎብኝዎች መምጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ይህ የዘርፍ አፈፅፀም ግን ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ከነበረው ሲነፃፀር 0.84 በመቶ ወይም ሰባት ሚሊዩን ዶላር ቅናሽ ሲመዘገብ የቱሪስቶች ቁትርም በ1979 ቀንሷል፡፡ ዋናዋናዎቹ ምክንያቶችም መንግስት የደነገገው የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ዘርፍን የበለጠ ተፅዕኖ ውስጥ መክተቱን በይፋ ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም ዲፕሎማቶች ካማንድ ፖስቱ ሳያሳውቁ ከ40 ኪሎ ሜትር በላይ እንዳይጎዙ መታገድ፡፡ በግጭቱ ወቅት በብሄራዊ ፓርኮች፣ በሎጆችና በሪዞርት ሆቴሎች ላይ በአብያታ ሻላ ብሄራዊ ፓርኮች፣ በባሌ ብሄራዊ ፓርክ በዙሪያቸው የሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወድመዋል፡፡ በተጨማሪም መንግስት በመላ ሃገሪቱ የጣለው የኢንተርኔት በተለይ የማህበራዊ ሚዲያዎች መዘጋታቸው የቱሪስቶችን ፍሰትና ገቢ ቀንሶታል፡፡የተለያዩ አገራቶችም ዜጎቻቸው ወደ ኢትዩጵያ እንዳይሄዱ መከልከላቸው ለዘርፉ ትልቅ አደጋ አስከትሎል፡፡

{5.3} የቆዳና ቆዳ ውጤቶች የውጪ ንግድ ገቢ፣ ‹‹የቆዳና ቆዳ ውጤቶች የውጪ ንግድ ገቢ ጉድለት አሳየ›› የ2009 ዓ/ም በጀት አመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የውጪ ንግድ አፈፃፀም ጉድለት ማሳየቱን የቆዳና ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ የኢንዱስትሪ ዘርፍ 49.48 ሚሊዩን ዶላር የውጪ ንግድ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ የተገኘው 26.09 ሚሊዩን ዶላር ነው፡፡ አፈፃፀሙ የዕቅዱን 52 .71 በመቶ ሆኖል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ተገኝቶ ከነበረው የ30.46 ሚሊዩን ዶላር ገቢ ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 14.36 በመቶ ወይም የ4.37 ሚሊዩን ዶላር ቅናሽ አሳይቶል፡፡

{5.4} የግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርቶች፣ ‹‹በዘንድሮ የምርት ዘመን 321 ሚሊዩን ኩንታል ዕህል ይጠበቃል›› የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተስፋዬ መንግስቴ፣ ዘንድሮ ከመሬት አንጻር 13 .1 ሚሊዩን ሄክታር ማሳ በሰብል ይሸፈናል በሚል መነሻ 321 ሚሊዩን ኩንታል የተለያዩ የሰብል ምርቶች ለማምረት አቅደናል፡፡ ከአንድ ሄክታርም 25 ኩንታል ይገኛል የሚል ታሳቢ ተይዞ ነው ወደ 2008/09 የምርት ዘመን የገባነው፡፡

| የምርት ዘመን ዓመት | ሚሊዩን ኩንታል |
|---|---|
| 2006/07 | 270 |
| 2007/08 | 266 ወይስ 226 |
| 2008/09 | 321 |

‹‹ኢትዩጵያ ባለፈው አስር ዓመታት በተከታታይ የምርት ዕድገት አስመዝግባለች፡፡ በተለይም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማብቂያ ወቅት የተገኘው 270 ሚሊዩን ኩንታል እህል ምርት ተጠቃሽ ነው፡፡የኤልኒና ክስተት በነበረበት ባለፈው ዓመት ደግሞ የ44 ሚሊዩን ኩንታል የምርት መቀነስ ታይቶል፡፡›› እንግዲህ ከ270 ሚሊዩን ኩንታል ላይ 44 ሚሊዩን ኩንታል ሲቀነስ 226 ሚሊዩን ኩንታል በ2007/08 ዓ/ም እንደሆነ ቁጥሩ ያሳብቃል፡፡ ከዚህ በመነሳትም በሃገሪቱ በ2008/09 ዓ/ም ከ15 ሚሊዩን ህዝብ ለአስቸኮይ ግዜ እርዳታ ተጋላጭ በነበረበትና በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ክልሎች በተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞና ተጋድሎ ወቅት 321 ሚሊዩን ኩንታል የተለያዩ የሰብል ምርቶች ይገኛል ተብሎ መጠበቅ ከንቱ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህ ተገኘ የሚማለውን የሰብል ምርቶች 321 ሚሊዩን ኩንታል ለህዝቡ ቁጥር 100 ሚሊዩን ህዝብ ብናካፍለው የአንድ ሰው የነፍስ

ወከፍ አመታዊ ድርሻ 3 ኩንታል መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ በዚህ መልክ ነው ሀገሪቱ ህዝብ በምግብ እራሳችንን የምንችለውና የዳቦ ቅርጫት የምንሆነው፡፡
በጋምቤላ ክልል ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ ሲካሄድ የነበረው የግብርና ኢንቨስትመንት ከ630 ሽህ ሄክታር መሬት የለማው 76 ሽህ ሄክታር ብቻ እንደሆነና፣መሬቱን የተረከቡት ባለሃብቶች 4.9ቢሊዩን ብር ከባንክ መውሰዳቸው በቀረበ ጥናት ቡድን ተረጋግጦል፡፡ ቦዘኔ ኢንቨስተሮች በአቆራጭ ለመበልጸግ የህዝቡን መሬት ተቀራምተው፣ከቀረጥ ነፃ መብት በመጠቀም ከብረዋል፣ከቦንኮች የወሰዱትን ብድር ዘርፈዋል፡፡ የግብርናው ኢንቨስትመንት ይሄ ግባ የማይባል ምርት የተመረተበት፣ የስራ ዕድል ያልፈጠረ የአገር ኃብት የጎዳ፣ ደኖች የተጨፈጨፉበትና የኢትዩጵያ ልማት ባንክ በቢለዩን ብር ኪሳራ እንደደረሰበት ተረጋግጦል፡፡ በ2008/9 የምርት ዘመን 321 ሚሊዩን ኩንታል ይመረታል የሚሉን!!!

## {5.5} የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን

የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን 500 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር ብድር ከቻይና ልማታ ባንክ (China Development Bank Corp.) ጋር ተፈራረመ፡፡ ባንኩ የቻይና ኮምኒስት ፓርቲ መንግስታዊ ንብረት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በብድሩ ሁለት ትልልቅ የስኳር ድፍድፍ ማጣሪያዎች ፋብሪካዎች ይገነባል፡፡ አንዱ ፋብሪካ በደቡብ ኢትዮጵያ ኦሞ ዞን ውስጥ የሚገነባ ሲሆን ሁለተኛው ፋብሪካ በሰሜን ምዕራብ አፋር ክልል ውስጥ በሜታል ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ኢትዮጵያዊ መንግስታዊ ድርጁትና በቻይና ኮምፐላንት ግሩፖ ኢንክ (China Complant Group Inc) የሚገነባ ሲሆን ምርቱን በ2025 እኤአ አስር እጥፍ ለማድረግ ታቅዶል፡፡
የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የወንጂ ሸዋ ፣የመተሃና የፊንጫ ስኳር ፋብሪካዎችን ጠቅልሎ በመያዝ በበላይነት እያስተዳደረ ይገኛል፡፡ኮርፖሬሽኩ በደቡብ ክልል ሰባት፣ በአማራ ክልል ሦስት፣ እንዲሁም በትግራይ ክልል አንድ(የአፋር ክልልን መሬት ወደ ትግራይ ክልል በመከለል የተወሰደ መሆኑን ልብ ይሎል) ፋብሪካን ጨምሮ በድምሩ 12 አዳዲስ ስኳር ፋብሪካዎችን የክልሎችን መሬት በፌዴራል መንግስት ስም በመንጠቅ በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡አስራ ሁለት የሸንካራ አገዳ እርሻና ፋብሪካዎች በመገንባት የስኳር ምርትን አሁን ካለው ምርት 265000 ሽህ ሜትሪክ ቶን ወደ 2.3 ሚሊዩን ሜትሪክ ቶን ከፍ በማድረግ ወደ ውጭ ሃገራት በተለይ ለአፍሪካ ቀንድ አገራት ለመላክ ሲሆን አገሪቶን በ2025 በዓለም ካሉት አስር የስካ፝Y ላኪ አገሮች ጎራ ለማስገባት በሚል የፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ተወጥኖል፡፡ የኢትዩጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን አጠቃላይ የግንባታ ስራ ወጭ 100 ቢሊዩን ብር (5.5 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር) እንደሚሆን ሲገመት ማሽነሪዎች ለመግዛት ግማሹ በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ይሻል፡፡

የኢትዩጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በአፋር ክልል ትንዳሆ 30 በመቶ ምርት በማምረት ላይ ሲገኝ በአሁኑ ግዜ በ394 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር ብድር ከህንድ አስመጭና ላኪ ባንክ(Export-Import Bank of India) በተገኘ ብድር የፋብሪካው ግንባታ ሥራ በህንድ(India's Overseas Infrastructure Alliance) በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡የኢትዩጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በጥናት ላይ የተመሰረተ ሥራ እንደማይሰራ በምሁራኖች ዘንድ ይታወቃል፡፡የምስራቅና ምዕራብ አፍሪካ የንግድና ልማት ባንክ (ፒቲኤ ባንክ) ለኢትዩጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን 25 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር ብድር ለመስጠት ስምምነታ ላይ ተደርሶል፡፡

## የሁለት ስኳር ፋብሪካዎች ግንባታዎች ግንባታ ተሰረዘ

የስኳር ኮርፖሬሽን በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ለመገንባት በዕቅድ ከያዛቸው አስር ስኳር ፋብሪካዎች ሁለቱን መሰረዙን አስታወቀ፡፡

- ኩራዝ ስኳር ፋብሪካ አምስት ፋብሪካዎች ለመገንባት ታቅዶ አሁን አንዱ ተቀንሶ አራቱ ፋብሪካዎች ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከ150 ሽህ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ እርሻ ለማልማት ታቅዶ 50 ሽህ ሄክታር ተቀንሶ 100 ሽህ ሄክታር ብቻ እየለማ ይገኛል፡፡
- በለስ ስኳር ፋብሪካ ሦስት ፋብሪካዎች ለመገንባት ታቅዶ አንዱን ፋብሪካ በመሠረዝ የሁለቱ ፋብሪካዎች ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከ75 ሽህ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ እርሻ ለማልማት ታቅዶ 25 ሽህ ሄክታር ተቀንሶ 50 ሽህ ሄክታር ብቻ እየለማ ይገኛል፡፡ የበለስ አንድና ሁለት እንዲሁም የኩራዝ አንድ ፋብሪካዎች ከአገር ውስጥ በተገኘ ብድር የሚገነቡ ሲሆን ፣ የኩራዝ ሁለት ፣ሦስትና አራት ፋብሪካዎች ግንባታ ደግሞ ከውጭ አበዳሪዎች በሰጡት ብድር የሚሰሩ

ኛቸው። ኮርፖሬሽኑ የሁለቱን ፋብሪካዎች ለመሰረዥ የተገደደው በአቅም ማነስ ነው። እቅዱ ወገቡ የሚያጎብጥ በመሆኑ ማድረግ የሚገባን ከኩራዝና ከበለስ አንዳንድ ፋብሪካዎችንና የሚለሙ እርሻዎችን መቀነስ ነበር ብለዋል የስኳር ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት ኮሚሽን ስራ አስፈፃሚ አቶ ጋሻው አይችሉም ። መንግስት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጨረሻ ላይ 2.25 ሚሊዮን ቶን ስኳር ለማምረት ግብ ጥሎ ነበር። ሜቴክ ስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ ስም 77 ቢሊዮን ብር መዝረፉ ልብ ይበሉ።

ቤዲሳ ግሩፕ የቱርክ ግዙፍ ኩባንያ በአንድ ቢሊዮን ዶላር የጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት ከፍተኛ ባለድርሻ ለመሆን እተደራደረ ነው። ቤዲሳ ግሩፕ ተባለው ግዙፍ የቱርክ ግዙፍ ኩባንያ፣ በአንድ ቢሊዮን ዶላር ካፒታል የጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክትን የ75በመቶ ድርሻ ለመውሰድ ድርድር መጀመሩን አስታወቀ። የበለስ አንድና ሁለት ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ ወጪ 1.4 ቢሊዮን ዶለሰር እንደሚደርስ ሲገመት ከዚህ ውስጥ ቤዲሳ ግሩፕ ከአንድ ቢሊን ዶላር ያላነሰውን ገንዘብ ለማቅረብ ተዘጋጅቶል። የተወሰነውን የፕሮጀክቱን ወጪ ከራሱ ለመሸፈን፣ ቀሪውን ከአገር ውስጥና ከውጭ ባንኮች ለማማላት እንዳቀደ አስታውቆል።

ህብር ስኳር ፋብሪካ ሕብር ስኳር አክሲዮን ማሕበር እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ አቀረበ፣ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን ፣ ጃዊ ወረዳ ውስጥ በሊዝ በገዛው ከ6000 ሄክትር በላይ መሬት ላይ የስኳር ፋብሪካ ገንብቶ ስኳር ለማምረትና ለገበያ ለማቅረብ አቅዶ ማህበሩ ከባንክ 1.5 ቢሊዮን ብር አክሲዮኖች መሸጥ የነበረበት ቢሆንም 100 ሚሊዮን ብር የማይበልጥ በመሸጡ ከባንክ ብድር ማግኘት እንዳልቻለ በአቤቱታው ተካቶል። ማህበሩ ፋብሪካውን ለማስተከል ከኢትዩጵያ ብረት ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር ተስማምቶ 25 ሚሊዮን ብር ቢከፍልም፣ በቦታው ላይ የመሠረት ድንጋይ ከተጣለበት ከሰኔ ወር 2007 ዓ/ም ድረስ ምንም ዓይነት ግንባታ አለማከናወኑን ገልፀዋል።ማህበሩ ከተቆቆመበት ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ ለተለያዩ ኪሳራዎች በመጋለጡ ፍርድ ቤቱ ማህበሩን በአስቸኮይ እንዲፈርስ ፍርድ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል።

{5.6} የብሸፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ (Bishoftu Automotive Industry(BAI) በወታደሩዊው መንግሥት በ1999 እኤአ በብሄራዊ መከላከያ ሚኒስትር አስተዳደር የተመሠረተ ፋብሪካ ነበር።በ2010እኤአ በህወኃት /ኢህአዴግ መንግስት ለብረትብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፐፖሬሽን (ብኤኮ) ተዘዋወረ።ፍብሪካው በአዲስ አበባ ከተማ 45 ኪሎ ሜትር ርቀት በደብረዘይት ከተም ውስጥ ይገኛል።ፍብሪካው የህዝብ ትራንስፖርት አውቶብሶች፣የከተማ ውስጥ አውቶብሶች፣የጭነት መኪኖች፣ፒክ አፕ መኪናዎችና ሲዩቪ መኪኖች ይገጣጥማሉ።በአሁኑ ግዜ ጀነራል ማናጀሩ ሌተናል ኮነሬል ገብረ መድህን ገብረ ሥላሴና ሻንበል አብዱል ፈታ ናስር ያባላሉ።

‹‹የአገር ውስጥ ተሽከርካሪ ምርት ዕጣ ፈንታ›› በአገሪቱ የተለያዩ የመንግስትና የግል የመኪና ማምረቻ እና መገጣጠሚያ ኩባንያዎች ያሉ ሲሆን የተለያዩ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎች እያመረቱ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ በገበያ ችግር ምክንያት የሚመረቱ ምርቶች የኩባንያዎቹን ካፒታል ይዘው እየተቀመጡ መሆኑ አጥኝዎቹ አስታውቀዋል።

የብሸፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ

- አንደኛ የከባድ ተሽከርካሪዎች ማምረቻ ፋብሪካው በቀን 52፣ በዓመት ከ12 ሽህ እስከ 15 ሽህ የሚሆኑ ከባድ ተሽከርካሪዎችን ያመርታል።
- ሁለተኛ በቀላል ተሽከርካሪዎች ማምረቻ ፋብሪካው ደግሞ ከ15 እስከ 20 ሽህ ፒክ አፕ ስቴሽን ዋገንና አነስተኛ የጭነት ተሽከርካሪዎች ያመርታል።
- ሦስተኛ የአውቶብስ ማምረቻ ፋብሪካው ደግሞ በዓመት ከሦስት እስከ አምስት ሽህ አውቶብሶችን የማምረት አቅም አለው።
- አራተኛ ኩባንያው ተሽከርካሪዎች ማምረቻ ብቻ ሳይሆን ሞተርና ብስክሌት እንዲሁም ከፊል አውቶማቲክ ከባድ ተሽከርካሪዎች የሚያመርቱ መሳሪያዎችን (ፕላንቶችን) ያመርታል።

የብሸፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ያጋጠሙት ችግሮች መኃከል በዋናነት የሚጠቀሱት

- የከባድና የቀላል ተሽከርካሪዎች የገበያ ዕጦት ምክንያት ምርቶች ተመርተው ካፒታል ይዘው እየተቀመጡ በመሆኑ ኩባንያው በሙ አቅሙ እንዳያመርት እንዳደረገው ታውቆል።

- በአሁኑ ወቅት በተለያየ ደረጃ ተመርተው ከሁለት ዓመት በላይ ያስቆጠሩ ከ430 በላይ ተሽከርካሪዎች በድርጅቱ ቅጥር ግቢ እንደሚገኙ የገልፃሉ፡፡
- ኢንደስትሪው ከሚያመርታቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት አንፃር በአገር ውስጥ ያለው የገበያ ድርሻ አንድ በመቶ እንኳን አይሞላም፡፡ ደንበኞቹም መንግስታዊ ዘርፎች ውስጥ የክልል ገጠር መንገዶች፣የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት፣የውሃ ሥራዎች፣አንበሳ አውቶብስ፣ሸገር ትራንስፖርት የድርጅቱ ምርት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ከ2012 እስከ 2016 እኤአ ከአገር ውስጥ ተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ኩባንያዎች 383 ተሽከርካሪዎች ተገዝተዋል፡፡
- ድርጅቱ ለ3ሺህ 200 የሥራ እድል የፈጠረ ሲሆን በገበያ እጦት የተነሳ ሠራተኛ የመቀነስ ስጋት አድሮባቸዋል፡፡
- የብሸፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ሌሎችም የአገር ውስጥ ተሽከርካሪ አምራቶች በዓለም ዐቀፍ ጨረታ ተወዳድረው ማሸነፍ አለመቻላቸው፣ የሚፈለገውን ምርት ማቅረብ አለመቻላቸው፣ምርቱ ሀገር ውስጥ ቢገኝም በአዋጅ መሠረት የገንዘብ መጠኑ የጨረታ ዘዴውን ስለሚወሰን በዓለም ዐቀፍ ጨረታ የውጭ ሀገር ምርቶች አሸናፊ የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ በመሆኑ ነው፡፡

ለማጠቃለል የብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) የገነባቸው አብዛኛዎቹ ፍብሪካዎች ልክ የብሸፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ዓይነት ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ እንደሚገጥማቸው ይታመናል፡፡ በአገሪቱ የተለያዩ የመንግስትና የግል የመኪና ማምረቻ እና መገጣጠሚያ ኩባንያዎች በሃገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያ ብቁ ተወዳዳሪ የሚያደርጋቸው አቅም መገንባት ባለመቻላቸውና በጥናት ላይ ተመስርተውና አስፈላጊው የገበያ ጥናት ሳይደረግ በመቋቋማቸው ለኪሳራ ተዳርገዋል፡፡ የውጭ ሃገራት የመኪና ማምረቻ እና መገጣጠሚያ ኩባንያዎች ለሶስተኛው ዓለም አገራቶች የሚያስተላልፉት ቴክኖሎጅ ኋላ ቀር የሆኑትን ፋብሪካዎች በመሆናቸው እንዲሁም በአመዛኙ የመኪኖቹ ጥሬ እቃ በውጭ ምንዛሪ ተገዝተው የሚመጡ በመሆናቸው ፋብሪካዎቹ አዋጭ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ የብሸፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ በህብረተሰቡ አቅም፣ ፍላጎትና የገንዘብ የመግዛት አቅም ላይ ተመስርተው ለገበሬው የማረሻ መሣሪያዎች፣ የልብስ ስፌት መኪኖች፣ የሽመና ማሽነሪዎች፣ የውኃ ጀነሬተሮች፣ቢሽክሌቶች፣ ባጃጆች ወዘተ በመሳሰሉት ማሽነሪዎች ሥራዎች ላይ ቢያተኩሩ የሃገር ውስጥ ገበያና ለምርት አቅርቦታቸው የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች ማግኘት ይችሉ ነበር፡፡

የአስቸኮይ ግዜ አዋጅ ይነሳ!!! ….ኮማንድ ፖስቱ ለፍርድ ይቀርባል!!!

መከላከያ ሠራዊቱ ወደ ካንፑ ይመለስ!!! …. መከላከያ ሠራዊት አፈሙዝህን ወደ ወያኔ አዙር!!!

የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!!!

ድል ለፋኖ ህዝባዊ ሠራዊት…. ዱሩ ቤቴ…….ነፃነቴ

በ2009 ዓ/ም ወያኔ በመላ ኢትዩጵያ በየቦታው በህዝባዊ ሽምቅ ውጊያ ድል ይመታል!!!

***ምንጭ***


1. ‹‹ግላዊ እና ብሄራዊ ኢኮኖሚያችን›› 2007፣ገፅ 145 ጌታቸው አሰፋው
2. The Ethiopian Herald (Saturday 3 December 2016)
3. ሪፖተር ጋዜጣ ታህሣሥ 12 ቀን 2009 ዓ/ም
4. Extracted from: The World Bank (2012) Remittances Data-inflow.
5. *Illegal Ethiopian Capital Flight*
6. አዲስ ዘመን ህዳር 23 ቀን 2009ዓ/ም
7. ሪፖርተር ጋዜጣ ህዳር 11 ቀን 2009ዓ/ም
8. አዲስ ዘመን ህዳር 28 ቀን 2009 ዓ/ም
9. **Ethiopia and Djibouti oil pipeline project set for construction** By Tesfa-Alem Tekle
10. አዲስ ዘመን መስከረም 7 ቀን 2009 ዓ/ም
11. ANDUALEM SISAY in Addis Ababa Wednesday, December 7 2016 at 18:41 comment
12. ***Zenawi and the devaluation of the birr፡ A layman's guide,Seid Hassan:2010-09-30, Issue 498, http://pambazuka.org/en/category/features/67399***
13. NEGATIVE EFFECTS OF DEVALUING THE BIRR
14. ***Abdur Rahman Alfa Shaban*** *with US DEPARTMENT OF STATE, Dec.8/2016*
15. *Exchange Rate* Pass-Through in Ethiopia: Mohammednur Behru: Addis Ababa University, June, 2012